
መዝሙር ጥራዝ ቁጥር



በማህበረ ቅዱሳን መዝሙርና ሥነ-ጥበባት ክፍል የተዘጋጀ

2002 ዓ.ም

ለሽያጭ የማይውል::

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

ፍጥረ ትን የፈጠረ፣ ነርሱንም በየዓለማቸው የሚመግብ (የሚገዛ) አምላክ ልዑል ግዚአብሔር በፍጥረ ቱ ለፍጥረ ቱ ራሱን ሲገልጥ፣ ክብሩን ሲያድል አለ፤ ይኖራልም (ሮሜ 6 ÷ 20)፡፡ ጌትነቱን ገልጠው ከሚመሰክሩለት ፍጥረ ት መካከል ሰውና መላ ክት አምል ኳቸውን በልብ የተገዙ ከማሰብ በላይ በቃላቸው አሰምተው፣ በአካላቸው ሰግደው አሸብሽበው የሚመሰክሩ ናቸው፡፡ ሰውን በአራቱ ባሕርያት (መሬት፣ ነፋስ፣ ሳት(ሙቀት) ና ው) አፀናው መሬ ዊ አካሉ ጋር ሕያዊት (የማትሞት)፣ ለባዊት (ዐዋቂ) ና ነባቢት (ተናጋሪ) ነፍስ ተዋሕዳለት አዋቂ ሆኖ ስለተፈጠረ አምላኩን ያውቃል፤ ያመልከዋል፤ ጌትነቱንም ይመሰክራል፡፡ ስለዚህ ለሰው የአምላኩ የ ግዚአብሔርን ሥም ማመስገንና ክብሩን መውረስ በጥንተ ተፈጥሮ የተሰጠው የመኖሩ ዓላማና ግብ ነው፡፡ ለአምላኩ ያለውን የፍቅር አምልኮ ከሚገልጥባቸው አገልግሎቶች መዝሙር (የዜማ ምስጋና) አንዱ ነው፡፡

በዚህ አገልግሎት ስከ ዓለም ፍፃሜ የሚነሳው ባለሃይማኖት ትውልድ ሁሉ በግሉም በማ በርም ሲያገለግል ንዳለና ንደሚኖር ከቅዱሳት መጻህፍትና ዛሬ የሆነ ካለውም የምንረዳው ውነት ነው፡፡ በየዘመኑ የተነሱ አበው ከአምላካቸው ፍቅር የተነሳ ርሱ ምስጋናው በ ርሱ ተወስኖ ንዳይቀር በጸጋ ለፍጥረ ቱ ንዳካፈለ (በፍጥረ ቱ ለመመስገን ንደፈቀደ) ሁሉ ነርሱም ያመሰገኑትን ምስጋና፣ የጸለዩትን ጸሎት ትውልድ ንዲያገለግልበትና ንዲከብርበት በቃልና በጽሑፍ አውርሰዋል፡፡

በሃይማኖት ጎዳና የቀደሙትን የተከተለ፣ ከኋላውም አዲስ ያስከተለ የሚጓዝ በየትኛውም ዘመን ያለ ክርስቲያን ትውልድም ይህን ማድረግ የሃይማኖት መብቱም ግዴ ውም ነው፡፡ የቀደመውን የወረስንና ያወረስን፣ አዲሱንም የፈጠርን ወደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የምንጓዝ ወራሾቻቸው የሚያሰኘንም ይኸ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ የተቀዳ አማኙን በሃይማኖት የሚያፅናና በምግባር የሚያንፅ የምስጋና ሥርዓት ባለቤት ናት፡፡ አባቶቻችን በብዙ መስዋዕትነት ያቆዩልን የጽሑፍና የዜማ ቅርስ በሃይማኖት ያለነውን ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ዜጋ የሚያስመካ ነው፡፡ ከዚህ ነባር ሀብት ጋር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትኩረትን ያገኘ የመጣውና በሰ/ት/ቤትና በማ በራት የሚሰባሰቡ ወጣቶች የሚገለገሉበት የአማርኛ መዝሙር አንዱ ነው፡፡ ከቤተክርስቲያኒቱ ሪክ ንደምንረዳው ዘመናዊ ትምህርትን ተከትሎ የተስፋፋው የወጣቶች መንፈሳዊ መነቃቃትና ሱ ፊ ካስከተላቸው ዐበይት ለውጦች ውስጥ የአማርኛ መዝሙር

ተጠቃሽ ነው።

በመሠረቱ ምዕመናን በጉባዔ በተሰበሰቡ ጊዜ በድርሳናትና በመዝሙራት መማማር በአባቶቻችን ሐዋርያት ዘመንም የነበረ ትውፊት መሆኑ አይዘነጋም።
በዚህ ረገድ የወጣቶች መዝሙር በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቅርብ ጊዜ ክስተት በመሆኑ ገና ብዙ የሚሠራበትና ትኩረትን የሚሻ ሆኖ ናገኘዋለን።
ከመነሻው ተመሳስለው የገቡ አሳቾች ንቅስቃሴ፣ ማዕከላዊ የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖር፣ የትምህርት ማነስ ወዘተ ባስከተሉት ችግር ይህ አገልግሎት ብዙ ፈተናዎችን አሳልፏል። አሁንም ከነችግሮቹ አሉ። ይህም ሲባል በብዙ ም መናን ሕይወት ላይ የ የውን መልካም ለውጥና የተሰሩ ስራዎችን በመዘንጋት አይደለም። ይህ ሲባል የሚ የው መልካም ውጤት የበለጠ ንዲያብብ ሲብስም ንድናጠራው ግን ከልብ ማሰብንና ተግቶ መስራትን ይጠይቃል ለማለት ነው። በካሴት ከሚቀርቡልን መዝሙራት ውስጥ ከትምህርተ ሃይማኖት ስከ ሥርዓትና ትውፊት የሚደርስ ስህተትና ግድፈት መስማት ከጀመርን ሰንብተናል። ችግሩ የሰፋ በመሔዱ በሚዲያዎች፣ በሴሚናርና በኮርስ ብዙ የምንነጋገርበት ርዕስ የመዝሙራችን ጉዳይ ሆኗል። ከዛሬ በነገ የተሻለ ይሆናል በሚል ተስፋም በብዙ የቤተክርስቲያን ልጆች ዘንድ ዛሬም ስለመዝሙርና ችግሮቹ መነጋገር አልተቋረጠም።

በኢ.ኦ.ተ.ቤ.ሰ.ት.ማ.መ ማ በረ ቅዱሳንም በዚህ ጉዳይ ላይ ከሚመለከ ቸው ጋር ከመሥራት በተጨማሪ በተለይ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ የቤተ ክርስቲያን ልጆችን በግቢ ጉባዔ በማሰባሰብ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ንዲሳተፉ ያበረ ል። ከዚህም አንዱ የተመረጡና ሥርዓተ-ቤተክርስቲያንን መሠረት ያደረጉ መዝሙራትን በመድበል ያዘጋጁ ለግቢ ጉባዔ አገልግሎት ንዲውል ማድረግ ነው። የዚህ ሥራ ዋና ዓላማ መዝሙራችን ትክክለኛውን አቅጣጫ ስኪይዝ ሊከሰቱ ከሚችሉ ስህተቶች ለመጠበቅ፣ ነባር መዝሙራት ንዳይረሱ ማስተላለፍ፣ አገልግሎቱን የጋራ ማድረግ ንጂ የሌሎችን የድካም ውጤት ማቃለል አይደለም። ስለዚህ የግቢ ጉባዔያት አስተባባሪዎች ዓላማውን ተረድተው ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። አዲስ መዝሙር በጥራዝ አልተካተተም ማለት አንድም አል የም አልያም ይቶ አላለፈም ይሆናል ንጂ የ ነ ገሌ ስለሆነ ተወግዟል ማለት አይደለም። በየጊዜው የሚወጡ ካሴቶችን መዝሙርም ንዳገኙ ለጉባዔ ማዋል በቅንነት ከምናደርገዉ ወደ ጎን የሚያስከትለውን ጉዳት ደግሞ በመረዳት ከስሜ ዊ አካሔድ መጠበቅ ከሁላችን ይጠበቃል።

ወንድሞችና ህቶች! ይህን በመረዳት በጥራዞቹና አብረው በተላኩት ካሴቶች በመ ገዝ የፍቅር አገልግሎትን ንድ ሰፉ ያሳሰብን ግጥሞችን በመፃፍ፣ ከተቻለም ዜማ በመድረስ፣ ነባር መዝሙራትን በማሰባሰብ በማዕከሎቻችሁ ጽ/ቤት በኩል የላካችሁ የማ በራችሁን መልካም

ዓላማ ንድትደግፉ ጥሪአችንን ናስተላልፋለን፡፡ ለወጣቶች መሰብሰብ ምክንያት የሆነው መዝሙራችን ለመበተን ንዳይሆን፣ ችግሮቹ ተወግደውለት ለመ ነጻችንና ለመጽና ችን ምክንያት ይሆንልን ዘንድ ሁላችን በበጎ ሕሊና ንሥራ፡፡ የአባቶቻችን አምላክ "ለሥሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ" (ዕብ 13÷15) በ ምነት ናቀርብለት ዘንድ ጸጋውን ያድለን፡፡ የ ግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን፡፡

በማ በረ ቅዱሳን ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ዋና ክፍል
የመዝሙርና ሥነ-ጥበባት ክፍል
2002 ዓ.ም

ማውጫ

መዝሙር ዘዘወትር 11

1. ተነሡ እንዘምር 11
2. የሕይወቱ መታመኛ 11
3. ዝማሬ ዳዊትን 12
4. ኑ እናመስግን 12
5. ቃልህ ሲነገር ልስማ 12
6. እልል ደስ ይበለን 12
7. ንሴብሖ ለእግዚአብሔር 12
8. ንጉሥ ውእቱ 12
9. ሠራዊተ መላእክቲሁ 13
10. እምኵሉ ይኄይስ 13
11. ታቦተ ሕጉ 13
12. አልቦ ዘከማየ 13
13. ድውይ ነን አንተ አድነን 13
14. ኵሉ ይሰግድ 13
15. ሰላም ዘአብ 14
16. ስብሐት ለአብ 14
17. የቅዱሳን አበው /ተዋሕዶ/ 14
18. በማስተዋል እንዘምር 15
19. ይትባረክ 15
20. የእውነት ብርሃን /አራራይ/ 15

መዝሙር በእንተ ዕለተ ትፍሥሕት (የደስታ ዕለት) 15

21. እንኳን ደስ ያላችሁ 15

መዝሙር በእንተ ዓውደ ዓመት 16

22. ጸልይ ኀበ አምላክ 16
23. እምሐሶ ለሄሮድስ 16
24. ራጉኤል እምሰማያት 16
25. ወአንተኒ ሕፃን 16

መዝሙር በእንተ ልደቱ ለእግዚእነ 16

26. ተወልደ ኢየሱስ 16
27. ርእይዎ ኖሎት 17
28. ይትፌሥሓ አድባረ ጽዮን 17
29. ቤዛ ኩሉ ዓለም 17
30. ዮም ተወልደ 17
31. በከመ ሰማዕነ 17
መዝሙር በእንተ ጥምቀቱ ለእግዚእነ 18
32. በፍስሐ ወበሰላም 18
33. በፍስሐ ወበሰላም እምሰማያት 18
34. ሥጋ ሰብእ መዋቱ 18
35. አስተርአየ ገሀደ 18
36. አንሶሰወ 18
37. ነድ ለማየ ባሕር 18
38. ክርስቶስ ተወልደ /ወለደነ/ 18
39. ክርስቶስ ተወልደ /አስተርእዮቱ/ 18
40. ግነዩ ለእግዚአብሔር 19
41. ኀዲጎ ተስዓ 19
42. አጥመቆ በማይ 19
43. መጽአ ቃል 19
44. ዮሐንስኒ ይቤ 19
45. ይእዜኒ ለሰላም 19
መዝሙር በእንተ ስቅለቱ ለእግዚእነ 20
46. አ ዘጥዕመ 20
47. ኧኸ በቀራንዮ 20
48. እፎ ቀሰፉከ 20
49. የእውነት ብርሃን /አራራይ/ 20
50. አምላክ ሆይ ልትሆን 20
51. ለቤተ ክርስቲያን ብለህ 21
መዝሙር በእንተ ትንሣኤሁ ለእግዚእነ 21
52. ዮም ፍስሐ ኮነ 21

53. ሰላም ሰላም 22
54. ለዛቲ ቤት 22
55. ጸጋ ዘአብ 22
መዝሙር በእንተ ደብረ ታቦር 22
56. አማን በአማን 22
57. የታቦር ተራራ 22
58. በስመ ዚአከ 22
መዝሙር ዘዘወትር ዘድንግል ማርያም 23
59. በምን በምን እንመስላት 23
60. እመቤቱ ጥላ ከለላዬ 23
61. ከደመና በታች እንዳይቀር ጸሎቱ 23
62. ትውልድ ሁሉ 23
63. ትብል ማርያም 23
64. በአምሳለ ዖፍ 24
65. ይእቲ እሞሙ ለሰማዕት 24
66. በጽሐ ሠናይ 24
67. ጽላት ዘሙሴ 24
68. ዘየሀይድ ዓይነ 24
69. እመ ብርሃን 24
70. ለመኑ እነግር ኃዘነ ልብየ 24
71. መሴኒ ርእያ 25
72. ልዑል ሠምራ 25
73. አ ማርያም 25
74. አ ድንግል 25
75. እንዘ ዘልፊ 25
76. በሰላም ንዒ 25
77. አስተርእዮ በሰማይ ኮነ 26
78. ኪዳንኪ ኮነ 26
79. ፀቃውዕ 26
80. ዕፀ ጳጦስ ዘሲና 26

81. ክብረ ቅዱሳን 26
82. ዕፀ ጳጦስ ይእቲ 27
83. ንጽሕት ቅድስት 27
84. ለሳውል ወኬፋ 27
85. ትርሲተ ወልድ 27
86. የዓለም ንግሥት የሆንሽው 27
መዝሙር በእንተ ብሥራት 28
87. ማርያም ደስ ይበልሽ 28
88. አብሠራ ወይቤላ 28
መዝሙር በእንተ ልደታ ለማርያም 28
89. አልብኪ ነውር 28
90. አዕይንታ ዘርግብ 29
91. ተወለደችልን 29
መዝሙር ዘዘመነ ጽጌ 29
92. አክሊለ ጽጌ 29
93. ረሀበ ወጽምዓ 29
94. ንግሥት እመቤቱ 29
95. አፉ ንህብ 30
96. ክበበ ጌራ ወርቅ 30
97. መዓዛ አፈዋት 30
98. ጎብረ ሐመልሚል 30
99. ሰላም ለኪ 30
100. ጽጌ አክሊለ ጽጌ 30
101. ክበበ ጌራ ወርቅ ጽሩይ 31
102. እንዘ ተጎቅፊዮ 31
መዝሙር በእንተ መስቀሉ ለእግዚእነ 31
103. መስቀሉሰ 31
104. ቤተ ክርስቲያን ርእየቶ 31
105. ዝንቱ መስቀል 31
106. እንተ ተሐንፀት በስመ 31

107. ኸኸ በመስቀልከ 32
108. ዘዕጣን አንጸረ 32
109. ይቤሎመ፡ ኢየሱስ 32
110. መስቀል ቤዛ ብዙኃን 32
111. ዮም በዓለ መስቀሉ 32
መዝሙር በእንተ ቅዱሳን መላእክት 32
112. እግዚኡ ረሰዮ 32
113. ሊቃነ መላእክት 32
114. የራማው ልዑል 33
115. ገብርዔል ግሩም 34
116. ገብርኤል መልአክ 34
117. ፍቁራኒሁ 34
118. ሱራፌል በግርማሆመ 34
መዝሙር በእንተ ቅዱሳን 34
119. የምእመናን አባት 34
120. ጸለዩ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ 34
121. ይቤሎ ጴጥሮስ 34
122. ተክለ ሃይማኖት ተወለዱ 35
123. አረጋዊ ምሉዓ ፍቅር 35
124. ደምፀ ወተሰብከ 35
125. ሰላም ለክመ 35
126. እስጢፋኖስ ሰማዕት 35
127. ሰአለ ሥርየተ ኃጢአት 35
128. እንዘ ይነብር በየማኑ 35
129. ግሩማን መላእክት 36
130. ዘአጽናእኮመ 36
131. ንዲን ብእሲቶ 36
132. ጥምቀተ አምጽአ 36
133. ለባርኮትነ ንኡ 36
134. በመንፈስ የሐውር 36

135. ያሬድ ካህን /ዕዝል ዜማ/ 36
136. በጽድቅ የሚያምኑብህ /ዕዝል ዜማ/ 37
መዝሙር በእንተ ጾም 37
137. አምላካችን ጾመልን 37
138. ዘጾመ ወጸለየ 37
መዝሙር በእንተ ንስሐ 38
139. አምላክ ሆይ ጠብቀኝ 38
140. ልመናዬን ስማኝ 38
141. ተነሡ እንዘምር 38
142. ስምዓኒ እግዚኦ ጸሎትየ 39
143. እንሂድ እንገስግስ 39
144. አማን በአማን 39
145. ታዛዥሆህ ልሁን /ዕዝል/ 40
146. አትራቀን /አሬሬይ/ 40
147. ደካማ ነኝ እኔ /አራራይ/ 41
148. በሰማይ የምትኖር አባታችን 41
149. ሃሌ ሉያ ሕያው ሆነህ የምትኖር 41
150. እስመ ለዓለም ምሕረቱ 42
መዝሙር በእንተ ቤተ ክርስቲያን 42
151. የድሆች መጠጊያ 42
152. እንኳን ደኅና መጣችሁ 42
153. ወደ ቤተ እግዚአብሔር 43
154. ሃሌ ሉያ አንጥላት 43
መዝሙር በእንተ ክረምት 43
155. ሰማያት ዘመሩ 43

መዝሙር ዘዘወትር

1. ተነሡ እንዘምር

ተነሡ እንዘምር/፪/
በአንድነት ሆነን በእልልታ/፪/ ኧኸ /፫/
ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር /፪/
ለኃያሉ ጌታ ለልዑል እግዚአብሔር
አሥፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር
ሁሉንም አለፍነው እግዚአብሔር ይመስገን
ሕዝቦች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል
ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል
ሰማይ ዙፋንህ ነው ምድር መረገጫህ
በዚህም በዚያም ቢሆን በሁሉም አንተው ነህ
በሄድንበት ሁሉ ትተለናለህ
ከፅንቅፋት ከድንጋይ ትሠውረናለህ
ስለመልካም ሥራህ አለብን ውለታ
ለማይነገረው የማዳን ስጦታ
ተመስገን እንበልህ ከጧት እሰከ ማታ
ሌሌ ምንም የለም የምንከፍልህ ጌታ
አምላክ ሆይ ስምህን ብንጠራው ብንጠራው
አልጠገብ አለን ምንኛ ጣፋጭ ነው
አቤት ያንተ ሥራ ያንተ ልግስና
ቢነገር አያልቅም ስምህ ነው ገናና
መልስ እንድናዘጋጅ ቶሎ ሳንጠራ
ሳለ አንደበታችን ምስጋናህን ያውራ
ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር
እሰከ ዘለዓለም ለስምህ እንዘምር

2. የሕይወቴ መታመኛ /በመ/መ/ ቅ/ገብርኤል ገዳም ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት ቁ.2/

የሕይወቴ መታመኛ የነፍሴ ተስፋ ቤዛዬ አምላኬ
መድኃኔዓለም ላመስግንህ እተጋለሁ ለውዳሴህ /፪/ኧኸ
መላእክቱ በሰማያት ቅዱስ /፫/ አንተ ነህ እያሉ
በክንፋቸው አሸብሽበው ይጠሩሀል በዝማሬያቸው /፪/ ኧኸ
ቅዱስ ዳዊት በበገና በእሥራኤል ሀገር /፪/
በተመሰጠ ወደ አርያም ዘልቆ ዘመረልህ አንተነትህን አውቆ /፪/ ኧኸ
ሕፃናትም አንተን አምነው በአህያ ተቀምጠህ ስትመጣ /፪
አፍ አውጥተው አመሰገኑህ ሆሳእና በአርያም አሉ /፪ ኧኸ
ሃሌ አለ ቅዱስ ያሬድ ጸናጽል መቋሚያ አንስቶ /፪/
ምስጋናህን ከልቡ ሸቶ በመንፈስህ ባንተ ተመርቶ /፪/ ኧኸ
ፈለጉንም ተከትለው ካህናት በሙሉ ቆመው /፪/
ይቀኛሉ ለቅዱስ ስምህ በማኅሌት በመመሰገኛህ/፪/ ኧኸ
እስትንፋስም ያለው ሁሉ ያመስግንህ አንተን በእውነት /፪/
ከልብ ሆኖ በንፁሕ እምነት እንደ እዝራ እንደ ዳዊት /፪/ ኧኸ

3. ዝማሬ ዳዊትን */ፈለገ ሠለስቱ ምዕት ማ በር/*

ዝማሬ ዳዊትን ተልዕኮ አርድእትን ቅዳሴ መላእክትን /፪/
የተቀበልክ አምላክ /፬/ የእኛንም ዝማሬ ተቀበል /፪/

4. ኑ እናመስግን */በደ/ይባቤ ቅ/ያሬድ ቤ/ክ ውሉደ ያሬድ ሰ/ት/ቤት/*

ኑ እናመስግን በዝማሬ በእልልታ
ጠላት ዲያብሎስን በሞቱ የረታ
ከእኛ ጋር ነውና የሠራዊት ጌታ
ጨለማው ኑሮ የስደት ሕይወት
በእግዚአብሔር ፍቅር ብርሀን በራበት
ባርነት ቀርቶ ነፃነት ወጣን
ልመናችንን እግዚአብሔር ሰማን
መሠናክሉን ክፉውን ፈተና
አልፈነው መጣን በአምላክ ጎዳና
አምላክ ከእኛ ጋር ስለነበረ
ዲያብሎስ አፍሮ ተዋረዶ ቀረ
የሚያስጨንቀን ዛሬ ተፈታ
የህዝቡን ዕንባ አበሰ ጌታ
በምህረቱ ስለጎበኘን
አምላካችንን ኑ እናመስግን

5. ቃልህ ሲነገር ልስማ

ቃልህ ሲነገር ልስማ ጌታ ሆይ እባክህ /፪/
ልቤን ክፈተው /፬/ የልድያን ልብ እንደከፈትከው /፪/

6. እልል ደስ ይበለን

እልል እልል ደስ ይበለን ልመናችንን አምላክ ሰማን /፪/
እናመስግነው/4/ ይገባዋል ሁሉን ፈፃሚ ነው ኧኸ /፫/

7. ንሴብሑ ለእግዚአብሔር

ንሴብሑ /፪/ ለእግዚአብሔር /፪/
ስቡሐ ዘተሰብሐ /፬/
እናመስግነው /፪/ እግዚአብሔርን /፪/
ምስጉን ነው የተመሠገነ /፬/

8. ንጉሥ ውእቱ

ንጉሥ ውእቱ ንጉሠ ሠላም /፬/
አምላክነ /፪/ መድኃኔዓለም /፪/
ንግሥት ይእቲ ንግሥተ ሰላም /፬/
ማርያም /፪/ ኪዳነ ምሕረት /፪/
ትርጉም፡- አምላካችን መድኃኔ ዓለም
የእውነትና የሰላም ንጉሥ ነው
የምህረት ቃል ኪዳን ድንግል ማርያም
የሰላም ንግሥት ናት

9. ሠራዊተ መላእክቲሁ

ሠራዊተ /፪/ መላእክቲሁ /፪/
ኧኸ ለመድኃኔ ዓለም /፪/ ይቀውሙ /፬/
ትርጉም፦ የመድ ኔ ዓለም የመላ ክት ሠራዊት በፊቱ ይቆማሉ

10. እምኵሉ ይኄይስ */ፋንቱ ወልዳ/*

እምኵሉ ይኄይስ በሥላሴከ ተአምኖ /፪/
በወላዲትከ /፪/ ወበ ወላዲትከ ተማኅፅኖ /፪/
ከሁሉም /፪/ ሥላሴን ነው ማመን ማመስገን /፪/
ወልድን በወለደች /፪/ ድንግል አማላጃችን በእርስዋ እንማፀን /፪/

11. ታቦተ ሕጉ */ሰ/ት/ቢ/ማ/መ/ቁ.3/*

ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር በካህናት ህፅርት ወበመንፈስ ቅዱስ ክልልት /፪/
ንጉሥኪ ጽዮን ኢይትመዋዕ ለፀር ወኢየ ድኃ ለሀገር /፪/
የሕግ ጽላቱ ለእግዚአብሔር በካህናት የታጠረች በመንፈስ ቅዱስም የተከለለች /፪/
ንጉሠሽ ጽዮን አይሸነፍም ለጠላት ሀገሪቱንም አይተዋትም /፪/
ትርጉም፦ 1. ሰሙ፡ ለጽዮን ለእሥራኤል ዘሥጋ
ወርቁ፡ ጽዮን ቤተ-ክርስቲያን ንጉሠሽ ክርስቶስ ስትፈተኚ
ቢያይም መንግሥተ ሰማያትን ከመሰጠት አይተውም
2. አማናዊት ጽዮን ማኅደረ መለኮት ድንግል ማርያም ናት

12. አልቦ ዘከማየ

አልቦ ዘከማየ /፪/ አበሳ ኃጢአት ገባሪ /፪/
ወአልቦ ዘከማከ /፫/ እግዚአብሔር መሐሪ /፪/
መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ዓለማተ ኵሉ ፈጣሪ /፪/
በደመ ገቦከ /፫/ ኃጢአትየ አስተሥሪ /፪/
ትርጉም፦ እንደ እኔ ያለ ኃጢአትን በደልን የሚሠራ የለም።።
እንደ አንተም እግዚአብሔር ይቅር ባይ የለም።።
ዓለምን ሁሉ የፈጠርክ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ሆይ
ከጎንህ በፈሰሰው ደምህ ኃጢአቴን አስተሥርይ

13. ድውይ ነን አንተ አድነን

ድውይ ነን አንተ አድነን } /፪/
መጻጉዕን የፈወስክ በልዩ ሥልጣንህ }
የሥጋ በሽታ በአንተ እንደ ተረታ /፪/ }
እኛም ተይዘናል በነፍስ በሽታ } /፪/
አድነን የሠራዊት ጌታ }

14. ኵሉ ይሰግድ

ኵሉ ይሰግድ ለሥላሴ /፪/ ኵሉ ይሰግድ /፪
ወይትቀነይ ኵሉ ለመንግሥተ ሥላሴ ለሥላሴ ኵሉ ይሰግድ /፪/
ትርጉም፦ ፍጥረት ሁሉ ለሥላሴ ይሰግዳል ለሥላሴ መንግሥት
ፍጥረት ሁሉ ይገዛል።።

15. ሰላም ዘአብ

ሃሌ ሉያ /፪/ ሰላም ዘአብ ወፍቅር ዘወልድ ሃይማኖት ዘመንፈስ ቅዱስ /፪/
ይኅድር ማዕከሌክሙ አምላከ ሰላም <u>ሰላም</u> /፪/ የሀሉ ምስሌክሙ
ሃሌ ሉያ /፪/ የአብ ሰላም የወልድ ፍቅር ሃይማኖት የመንፈስ ቅዱስ
ይደር በመካከላችሁ የሰላሙ አምላክ <u>ሰላም</u> /፪/ ከእናንተ ጋር ይሁን /፪/

16. ስብሐት ለአብ */ሲ.መ.ኪነ ጦበብ ቁ.1/*

ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ
ሰብሐት ለመንፈስ ቅዱስ
ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም
ምስጋና ከማቅረብ <u>ከቶ አንወሰንም</u> /፪/
ዛሬም ወደ ፊትም ደግሞም ለዘለዓለም
ከዚህ ከማራኪው ከአስጨናቂው ዓለም
የጠራ ይድናል <u>የፈጣሪውን ስም</u> /፪/
በእውነት ያለ ሀሰት ያለ ጥርጥር
ከቶ መድኃኒቱን የሚጠላ የለም
ኑሮአችን እንዲያምር <u>አንድነታችንም</u> /፪/
ሊኖረን ይገባል ፍቅርና ሰላም
ያልከውን አስበህ እናንተ ሁላችሁ
ሁለት ሦስት ሆናችሁ <u>በስሜ ካላችሁ</u> /፪/
እኔም እገኛለሁ በመካከላችሁ
አቤቱ አምላክ ሆይ እንለምንሃለን
እንድትገኝልን <u>በመካከላችን</u> /፪/
ይኸው ተገኝተናል ሁለት ሦስት ሆነን

17. የቅዱሳን አበው /ተዋሕዶ/ */ለመ/መ/ ቅ/ገብርኤል ገዳም ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት ቁ.2/*

የቅዱሳን አበው አሠረ ፍኖት
የጽድቅ አክሊላቸው የሰማዕታት
ተዋሕዶ የቀናች ሃይማኖት
አንቺ ነሽ የነበርሽ ከጥንት
ሚጠት የሌለብሽ ውላጤ ጎድረት
ትድምርት የማትዪ ቱሳሄ ፍልጠት
ትዋሕዶ የቄርሎስ ትምህርት
በእውነት ንጽሕት ሃይማኖት
ከተራራ ጫፍ ላይ የተሠራች መንደር
እንዴት ይቻላታል ከሠው ልትሠወር
ትዋሕዶ ከፍ ከፍ ያልሽ ነሽ
በእውነት አቻ የሌለሽ
ወልደ አብ ወልደ ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስ
ብለሽ አስተማሪ ቀጥተኛ መንገድ
ትዋሕዶ እውነተኛ ሃይማኖት
በእውነት መንገድ የድኅነት

18. በማስተዋል እንዘምር /በመ/መ/ ቅ/ገብርኤል ገዳም ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት ቁ.2/

እግዚአብሔር ለምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና
በማስተዋል እንዘምር እናቅርብለት ምስጋና /፪/
ቅዱስ ዳዊት በተመስጦ ሲዘምር
በሳአል ላይ ዘወትር የሚያድር
ርኩስ መንፈስ ይለቀው ነበር
ቅዱስ ጳውሎስ በአደባባይ መሠከረ
በእስር ቤትም ሆኖ በማስተዋል ዘመረ
ከልብ በማመስገኑም የወኅኒው በር ተሰበረ
አስተውሉ የሚዘምር ቅዱስ ያሬድን አንዘንጋ
አልታወቀውም ደሙ ሲፈስ በጦር እግሩ ሲወጋ
በተመስጦ ደርሷልና ከአልፋና ያሜጋ
ከፈጣሪ ዘንድ እንዲደርስ ጸሎታችን
በማስተዋል እናመስግን የእውነት ይሁን ዝማሬአችን
በማስተዋል እንዘምር ከልብ ይሁን ምስጋናችን
አዝ----------

19. ይትባረክ

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እሥራኤል
ዘገብረ ዐቢየ ወመንክረ ባሕቲቱ
ወይትባረክ ስመ ስብሐቲሁ ቅዱስ
ወይምላዕ ስብሐቲሁ ኵሉ ምድረ ለይኩን ለይኩን
ትርጉም፦ የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ
ታላቅ ድንቅ ሥራ ብቻውን የሠራ
ቅዱስ ስሙ ይባረክ
ምስጋናው ምድርን ሁሉ ይምላ ላይ ይሁን ይሁን

20. የእውነት ብርሃን /አራራይ/

ብርሃን የእውነት ብርሃን ጨለማን ያጠፋ
ሞተ ነፍስን የሻረ ክርስቶስ የዓለም ተሰፋ
ስለ ሰው ፍቅር ስለ ሰው ልጅ ክብር
ሥጋን ለብሶ ሰው ሆነ ከአዳም ልጅ ዘር
ምን ዕፁብ ድንቅ ነው ላሰበው
ምን ግሩም ድንቅ ነው የፈጣሪ ሥራው
እርሱ አምላክ ሲሆን የዓለም መድኅን
ተቀብሏልና ፍዳና ሞትን ዓለምን ሁሉ ለማዳን

መዝሙር በእንተ ዕለተ ትፍሥሕት (የደስታ ዕለት)

21. እንኳን ደስ ያላችሁ

እንኳን ደስ ያላችሁ /፪/
መልእክተ ዮሐንስ ሀ ሁ ብላችሁ
ፊደል ቆጥራችሁ ከእነ የኔታ ጠዋትና ማታ

ተመላልሳችሁ ለዚህ በቃችሁ
የአምላክ ቸርነት ረቂቅነት
ይህ ነው ችሮታው ከሀፃንነት እሰከ አዋቂነት
ዓመታት ቆጥሮ ለዲፕሎም /ዲግሪ/ መብቃት
የተዋሕዶ ልጆች እናንት ሁላችሁ
የዕውቀት ካባ ጃኖ ለብሳችሁ ደስ ማለታችሁ
አደራ እንዳትረሷት ቤተ ክርስቲያንን
አንዲት ተዋሕዶ አደራችሁን
አዝ----------

መዝሙር በእንተ ዓውደ ዓመት

22. ጸልይ ኀበ አምላክ

ጸልይ ኀበ አምላክ /፪/ ራጉኤል መልአክ /፪/
ዐውደ ዓመት ከመ ይትባረክ /፬/
ትርጉም፦ ዐውደ አመቱ እንዲባረክ ራጉኤል ሆይ ወደ አምላክ ጸልይ

23. እምሔሶ ለሄሮድስ

እምሔሶ ለሄሮድስ ይብላዕ መሐላሁ /፪/ እም ያምትር ርዕሶ ለዮሐንስ /፪/
ዐቢይ ነቢይ /፪/ ሰባኬ ወንጌል/፬/
ትርጉም፦ ሄሮድስ ዋና ነቢይ የሆነውንና የጥምቀት ሰባኪ
የዮሐንስን አንገት ከሚያስቆርጥ መሐላውን ቢበላ ይሻለው ነበር

24. ራጉኤል እምሰማያት *(ፋንቱ ወልዴ)*

ራጉኤል እምሰማያት /፪/
እም ኀበ ሳዕል ወረደ እምልዑላን /፬/
ትርጉም፦ ራጉኤል ከሰማያት ከፍ ካለ ቦታ ወረደ

25. ወአንተኒ ሕፃን */ደብረ ሰሚን ተክለሃማኖት/*

ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል/፬/
አርኩ ለመርዓዊ ትሰመይ/፪/ ነቢየ ልዑል/፪/
ትርጉም፡ አንተ ሕፃን የልዑል ነቢይ የሙሽራው ክርስቶስ
መንገድ ጠራጊ ትባላለህ /ትሰኛለህ/

መዝሙር በእንተ ልደቱ ለእግዚእነ

26. ተወልደ ኢየሱስ

ተወልደ ኢየሱስ በቤተ ልሔም /፪/ ዘይሁዳ በቤተ ልሔም /፪/

አዋልደ ጢሮስ <u>አሜሃ ይሰግዳ</u> /፪/ በቤተ ልሔም
ትርጉም፡ ኢየሱስ በይሁዳ በቤተልሄም ተወለደ የጢሮስ ሴት ልጆች ያን ጊዜ ይሰግዱለታል።

27. ርእይዎ ኖሎት

ዮም ሰማያዊ በጎል ሰከበ ለዘተወልደ እምቅድስት ድንግል /፪/
ርእይዎ ኖሎት /፪/ <u>አእኰትዎ መላእክት</u> /፪/
ትርጉም፡ ዛሬ ከቅድስት ድንግል የተወለደውን እረኞች አዩት መላእክት አመሰገኑት

28. ይትፌሥሓ አድባረ ጽዮን */ሰ.ት/ቤት.ማ. ቁ.2/*

ይትፌሥሓ አድባረ ጽዮን ወይትሐሠያ አዋልደ ኢትዮጵያ /፪/
እስመ ተወልደ ብሑተ ልደት መድኃኔ ዓለም በኢየሩሳሌም መድኃኔ ዓለም /፪/
ትርጉም፡ የጽዮን ተራራሮች ይደሰታሉ፤ የኢትዮጵያም ልጆች ሐሤትን ያደርጋሉ፤
በልደቱ ብቸኛ የሆነ መድኃኔ ዓለም በኢየሩሳሌም ተወልዷልና።

29. ቤዛ ኩሉ ዓለም

ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ
ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ
የዓለም ሁሉ መድኃኒት ዛሬ ተወለደ
የዓለም ሁሉ መድኃኒት ዛሬ ተወለደ

30. ዮም ተወልደ

ዮም ተወልደ መድኃኔ ዓለም
ዮም ተወልደ ከሣቴ ብርሃን
ትርጉም፡- የዓለም መድኃኒት ዛሬ ተወለደ
ብርሃንን የሚገልጥ /የብርሃን ጌታ/ዛሬ ተወለደ

31. በከመ ሰማዕነ *(ማኅ/ቅ/ቁ 6)*

በከመ ሰማዕነ ከማሁ ርኢነ
በሀገረ እግዚአ ኃያላን በሀገረ አምላክነ
አዳምን ሊያደነው ቃል እንደገባለት
በመስቀል ተሰቅሎ ቤዛ ሊሆንለት
እንደተናገረ ከሰማይ ወረደ
በሰው አካል ታየ በጎል ተወለደ
ነቢያቱ እንዳዩ በትንቢት መነፅር
የያዕቆብን ኮከብ የእሴይን ስር በትር
እኛ ግን በአካል ተገልጦ አየነው
በግዕዘ ህፃናት በጎል አገኘነው
ከህዝቅኤል ምሥራቅ ፀሐይ እንዲወጣ
ወገኑን ሊታደግ መድኅን እንዲመጣ
ነቢያቱ እንዳሉ እኛም እንደሰማን
በአምላካችን ሀገር የሆነውን አየን

መዝሙር በእንተ ጥምቀቱ ለእግዚእነ

32. በፍስሐ ወበሰላም

በፍስሐ ወበሰላም /፪/
ወረደ ወልድ /፪/ ውስተ ምጥማቃት /፪/
ትርጉም፡ በደስታና በሰላም እግዚአብሔር ወልድ ወደ መጠመቂያ ወረደ

33. በፍስሐ ወበሰላም እምሰማያት

በፍስሐ ወበሰላም ምሰማያት /፪/
ወረደ ወልድ ውስተ ምጥማቃት /፬/
ትርጉም፡-በደስታና በሰላም እግዚአብሔር ወልድ ወደ መጠመቂያ ወረደ

34. ሥጋ ሰብእ መዋቴ

ሥጋ ሰብእ መዋቴ /፬/
ወገብረ መንጦላዕተ /፰/
ትርጉም፡ የሚሞተውን የሰውን ሥጋ
መሠወሪያው አደረገ (ተዋሐደ)

35. አስተርአየ ገሀደ

አስተርአየ ገሀደ አስተርዓየ እንዘ ህፃን /፪/
እንዘ ህፃን ልህቀ/፪/ በዮርዳኖስ ተጠምቀ እንዘ ሕፃን /፪/
ትርጉም፡ በግልጥ ታየ እንደ ህፃናት ቀስ በቀስ አደገ በዮርዳኖስ ተጠመቀ::

36. አንሶሰወ

አንሶሰወ /፪/ ወአስተርአየ /፪/
በዮርዳኖስ ኧኸ ተጠምቀ በዮሐንስ /፬/
ትርጉም፡- ተመላለሰ በግልጥ የ በዩርዳኖስ ወንዝ በዩሐንስ ጅ ተጠመቀ::

37. ነድ ለማየ ባሕር */ሰ.ት/ቢ.ት.ማ.መ.ቁ.2/*

ነድ ለማየ ባሕር ከበቦ /፪/
ማየ ባሕር ኀበ የሐውር ፀበቦ /፬/
ትርጉም፡- እሳት የባሕሩን ውሃ ከበበው ባሕሩም የሚሄድበት ጨነቀው::

38. ክርስቶስ ተወልደ */ወለደነ/*

ክርስቶስ ተወልደ እሰይ
ክርስቶስ ተጠምቀ በማይ
ወለደነ ዳግመ እማይ /፪/ ዳግመ /፪/ ወለደነ ዳግመ እማይ
ትርጉም፡- ክርስቶስ ተወለደ፣ ክርስቶስ ተጠመቀ ዳግም ከውሃ ወለደን

39. ክርስቶስ ተወልደ */አስተርእዮቱ/*

ክርስቶስ ተወልደ ወተጠምቀ /፪/
አስተርእዮቱ አማን አስተርእዮቱ /፪/
ትርጉም፡- ክርስቶስ ተወለደ ተጠመቀ መገለጡም እውነት ነው::

40. ግነዩ ለእግዚአብሔር

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ⷗ሬ /ⷩ/
እስመ ለዓለም ምሕረቱ እስመ ለዓለም /ⷪ/
እናመስግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ /ⷩ/
የዓለም ቤዛ ነውና የማኅፀንሽ ፍሬ /ⷪ/
ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከአንቺ ተወልዶ /ⷩ/
መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን ለመቀደስ /ⷪ/
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ዕዳችንን ፋቀ /ⷩ/
በቸርነቱ አወቀን ከበደል አራቀን /ⷪ/
በድንግልና የወለድሽው የአንቺ ጽንስ /ⷩ/
የድኩማኖች ብርታት ነው የሕሙማን ፈውስ /ⷪ/
ስምሽን የጠራ ዝክርሽንም ያዘከረ /ⷩ/
በመንግሥተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ /ⷪ/
ብርሃነ መለኮት ያደረብሽ አዳራሽ /ⷩ/
ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ /ⷪ/
እመቤታችን እናታችን ማርያም /ⷩ/
የተማጸነሽ ይኖራል ለዘለዓለም /ⷪ/

41. ንዲጎ ተስዓ

⷗ዲጎ ተስዓ ወተስዓተ <u>ነገደ</u> /ⷩ/
<u>ማዕከለ ባህር</u> /ⷩ/ ቆመ ማዕከለ ባህር /ⷩ/
ትርጉም፦ዘጠና ዘጠኙን ነገደ መላእክት ትቶ በባሕር መካከል ቆመ

42. አጥመቆ በማይ

አጥመቆ በማይ /ⷫ/
ዮሐንስ /ⷭ/ አጥመቆ በማይ
ትርጉም፦ ዮሐንስ መድ ኢታቾንን በውሃ አጠመቀው

43. መጽአ ቃል

መጽአ ቃል /ⷩ/ እም ደመና ዘይብል /ⷩ/
እምደመና ዘይብል /ⷭ/ ዝንቱ ወልድየ /ⷩ/
ትርጉም፦ ዘጠና ዘጠኙን ነገደ መላእክት ትቶ በባሕር መካከል ቆመ

44. ዮሐንስኒ ይቤ

ዮሐንስኒ /ⷩ/ ይቤ ዘአጥመቆ በዮርዳኖስ /ⷩ/
ርኢክዎ ወስእንኩ ጠይቆቱ ስእንኩ /ⷩ/
ትርጉም፡ ትርጉም ፤- በዮርዳኖስ ጊታን ያጠመቀው ዮሃንስ
ጊታዬን አየሁት እርሱን መርምሪ ልደርስበት አልቻልኩም አለ፤፤

45. ይእዜኒ ለሰላም

ይ ዜኒ ለሰላም <u>ንትለዋ ለሰላም</u> /ⷩ/
ተጠምቀ ነዋ መድ ኄ ዓለም መድ ኒነ መድ ኄ ዓለም /ⷩ/

መዝሙር በእንተ ስቅለቱ ለእግዚእነ

46. ኦ ዘጥዕመ /ማኅበረ ቅዱሳን ቁ.4/

ኦ ዘጥዕመ ሞተ በሥጋ /፫/
ሲጠማ ለኖረው በሲያል በረሃ
ከጎኑ ሊያጠጣው የሕይወትን ውሃ
በክብር ሊመልሰው በኤዶም ሊያኖረው
በመስቀል ተሰቅሎ ሊያድነው ከፍዳ
ከዙፋኑ ወርዶ ለብሶ ከለሜዳ
በሰው እጅ ተመትቶ በችንካር ተወግቶ
ግዕዛንን ሊሰብክ ወደ ሲኦል ወርዶ
ምውቱን ሊያድነው ራሱን አዋርዶ
ሊቀድስ በደሙ ሊያከብር በስሙ
አዝ----------

47. ኧኸ በቀራንዮ /ዲ/ን መገርሳ/

ኧኸ በቀራንዮ ኧኸ በፈሰሰው ደምህ /፪/
ኧኸ በክቡር ስምህ አምላክ ሆይ ማረን እባክህ /፪/

48. እፎ ቀሰፉከ /ምንጭ መልክዓ መድኃኔ ዓለም/

እፎ ቀሰፉከ ካህናተ ይሁዳ ወሌዊ /፪/
መድኃኔ ዓለም /፪/ ሕፃን ወአረጋዊ /፪/
ትርጉም፡- ሕፃኑና አረጋዊውም የይሁዳና የሌዊ ካህናት
መድኃኔዓለም ሆይ እንዴት ገረፉህ

49. የእውነት ብርሃን /አራራይ/

ብርሃን የእውነት ብርሃን ጨለማን ያጠፋ
ሞተ ነፍስን የሻረ ክርስቶስ የዓለም ተሰፋ
ስለ ሰው ፍቅር ስለ ሰው ልጅ ክብር
ሥጋን ለብሶ ሰው ሆነ ከአዳም ልጅ ዘር
ምን ዕፁብ ድንቅ ነው ላሰበው
ምን ግሩም ድንቅ ነው የፈጣሪ ሥራው

50. አምላክ ሆይ ልትሆን (ማኅ/ቅ/ቁ 6)

አምላክ ሆይ ልትሆን ቤዛ ለሠው ልጅ
መከራን ተቀበልክ በግፈኞች እጅ
የአይሁድ ማኅበር በአንተ ላይ መከሩ
በሞት ሊያሰቀጡህ ሁሉም ተባበሩ
በሐሰት ወንጅለው ሸንጎቸው አቆሙህ
በግፍ ዱላ መትተው ምራቅን ተፉብህ
ከገዢው ፊት ቀርበው ሕዝቡን አባበሉ
በርባንን አስፈቱ አንተን ሊያሰቅሉ
አሳልፎ ሰጠህ ጲላጦስ ፈትኖ
ገርፈው እንዲሰቅሉህ ጽድቅህ በደል ሆኖ

በአምስቱ ቅንዋት ቸንክረው በመስቀል
ቀራንዮ አዋሉህ በሽፍቶች መካከል
ውሃ ብትለምን የውሆች ባለቤት
ሀሞትን አጠጡህ የግፋቸው ብዛት
ያንን ሁሉ መከራ በትዕግስት ፈፅመህ
ነፍስህን ከሥጋህ በፈቃድህ ለየህ
የትዕግስትህን ብዛት መላእክት አደነቁ
ለሰው ልጅ ያለህን ፍቅርህን አወቁ

51. ለቤተ ክርስቲያን ብለህ /ማኅ/ቅ/ቁ6/

ዘበእንቲኣሃ ለቤተ ክርስቲያን ተጸፋእከ በውስተ ዓውድ
ከመ ትቀድሳ በደምከ ክቡር
ዘበእንቲኣሃ ዝግሃታተ መዋቅሕት ፆረ ወተኣገሠ ምራቀ
ርኵሰ እንዘ ኣልቦ ዘኣበሰ ኣምላክ ዲበ ዕፀ መሰቀል ተሰቅለ
ለቤተ ክርስቲያን ብለህ ልትቀድሳት በደምህ
በአደባባይ በጥፊ ተመታህ
ንጹሕ ክርስቶስ በአዳም ጥፋት ልትወቀስ
በከንቱ ልትከሰስ አመላለሱህ
ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ
ሁሉን ቻይ ሳለህ ምንም ማድረግ ሳይሳንህ
በአይሁድ እጅ ተገረፍክ
ወዮ ወሰን የሌላት ትዕግሥትህ
ስለ እኛ ብለህ መከራን ተቀበልክ
ምንም በደል ሳይኖርብህ
አምላክ በእንጨት መስቀል ላይ ሰቀሉህ

<u>መዝሙር በእንተ ትንሣኤሁ ለእግዚእነ</u>

52. ዮም ፍስሐ ኮነ /ሃሌ ሉ/

ዮም ፍስሐ ኮነ በሰንበተ ክርስቲያን እስመ ተንሥአ
ክርስቶስ እሙታን ቀደሳ ወአክበራ እምኵሎን መዋዕል
አልፀላ አማን ተንሥአ እምነ ሙታን

ዮም ፍስሐ ኮነ በሰንበተ ክርስቲያን እስመ ተንሥአ
ክርስቶስ እሙታን
<u>ቀደሳ ወአክበራ</u> /፪/ እምኵሎን መዋዕል

ዛሬ ደስታ ሆነ በሰንበተ ክርስቲያን ተነሥቷልና ክርስቶስ ከሙታን
ቀደሳት አከበራት /፪/ ከፍም አደረጋት ከሁሉም ዕለታት

ትርጉም: ዛሬ በክርስቲያን ሰንበት ደስታ ሆነ ክርስቶስ ከሙታን
ተነሥቷልና ቀደሳት አከበራት ከፍ ከፍ አደረጋት ከሁሉም ዕለታት

53. ሰላም ሰላም

ሰላም ሰላም/፪/
እምይእዜሰ ይኩን ሰላም /፬/
ሰላም ሰላም /፪/
ከእንግዲህስ ይሁን ሰላም /፬/

መዝሙረ ዘጸራቅሊጦስ

54. ለዛቲ ቤት

ለዛቲ ቤት ሐነፃ ወልድ /፪/
ወፈፀማ መንፈስ ቅዱስ /፬/
ይህችን ቤት ወልድ አነፃት /፪/
መንፈስ ቅዱስም ፈፀማት /፬/

55. ጸጋ ዘአብ

ጸጋ ዘአብ ሒሩት ዘወልድ ሱታፌ ዘመንፈስ ቅዱስ /፪/
ተውህቦሙ /፫/ ለሐዋርያት /፪/
ትርጉም፡ የአብ ጸጋ የወልድ ቸርነተ የመንፈስ ቅዱሰ አንድነት /በረከት/ ለሐዋርያት ተሰጣቸው፡
/ለጸራቅሊጦስ ለሐዋርያት በዓል የሚባል/

መዝሙር በእንተ ደብረ ታቦር

56. አማን በአማን

አማን በአማን /፬/
ተሰብሐ በደብረ ታቦር /፬/
ትርጉም፡ እውነት በእውነት በደብረ ታቦር ተመሰገነ::

57. የታቦር ተራራ

የታቦር ተራራ በጣም ደስ ይብልሽ /፪/
እግዚአብሔር መለኮቱን ስለገለጠብሽ /፬/

58. በስመ ዚአከ

በስመ ዚአከ ይትፌሥሑ ዮም /፪/
ታቦር ወአርሞንኤም /፬/
ትርጉም፡ ታቦርና አርሞንኤም በስምህ ዛሬ ደስ ይላቸዋል::

መዝሙር ዘዘወትር ዘድንግል ማርያም

59. በምን በምን እንመስላት */ሰኮቴት ቁ.1/*

በምን በምን እንመስላት ድንግል ማርያምን
ምሳሌ የላትም/፪/ ክብሯን የሚመጥን /፪/
የሙሴ ጽላት ነሽ የምሕረት ቃል ኪዳን
የያዕቆብ መሰላል የአብርሃም ድንኳን
የብርሃን መውጫ የኖኅ ድንቅ መርከብ
የመላእክት እህት የሩኅሩኃን ርግብ /፪/
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
የዕዝራ መሰንቆ የጌዴዎን ፀምር
ድንግል እመቤት ናት የጻድቃኖች በር
ሆና የተገኘች የአምላክ ማኅደር /፪/
የቅዱሳን እናት የዓለም ንግሥት
ችላ ተሸከመች መለኮት እሳት
ብርሃን ትሁነን ጨለማን ገላልጣ
አማልዳ ታስምረን ከዚህ ዓለም ጣጣ /፪/
ከማር ይጣፈጣል የድንግል መዓዛ
አምላክን አቅፋለች በሁለት እጇ ይዛ
ዓለሙ ሁሉ የዳነው በልጅሽ ነውና
እናታችን ጽዮን ይድረስሽ ምስጋና /፪/
አዝ---------

60. እመቤቴ ጥላ ከለላዬ

እመቤቴ ጥላ ከለላዬ ረዳቴ የገነት ሙሽራ /፪/
የገነት ሙሽራ/፫/ ማርያም የልዑል ማደሪያ /፪/

61. ከደመና በታች እንዳይቀር ጸሎቴ

ከደመና በታች እንዳይቀር ጸሎቴ
አሳርጊው /፪/ ድንግል እመቤቴ /፬/

62. ትውልድ ሁሉ */ማኅበረ ቅዱሳን ቁ.6/*

ትውልድ ሁሉ ብፅዕናሽን ክብርሽን ሁልጊዜ ያደንቃሉ
መመኪያችን መጠጊያችን ተስፋችን አንቺ ነሽ እያሉ /፪/
ያገኙሻል ያከብሩሻል ፍጥረታት በሙሉ /፬/

63. ትብል ማርያም

ኧኸ ትብል /፫/ ማርያም አዋልደ ኢየሩሳሌም
ፃአ ትርአያ /፫/ ኀበ ንጉሥክን /፪/ መድኃኔ ዓለም
አክሊለ አስተቀጸልዎ ዲበ እፅ ሰቀልዎ /፪/

ትርጉም፡- ማርያም የኢየሩሳሌም /የቤተ ክርስቲያን/ ልጆች ሆይ
ወደ ንጉሣችሁ ወደ መድኃኔዓለም ታዩት ዘንድ ውጡ ትላለች
የሾህ አክሊልን አቀዳጆት በእንጨትም ላይም ሰቀሉት እያለች

64. በአምሳለ ያፍ

በአምሳለ ያፍ /፪/ ፀአዳ ርግብ ትመስል ማርያም ድንግል /፪/
ይእቲኬ ደመና ቀሊል ማርያም ድንግል እሙ ለእግዚአብሔር /፪/
ትርጉም፦ ድንግል ማርያም እንደ ነጭ ርግብ የወፍ አምሳያ ትመስላለች
ይህቺውም ድንግል ማርያም ፈጣኗ ደመና የእግዚአብሔር እናት ናት

65. ይእቲ እሞሙ ለሰማዕት

ይእቲ እሞሙ ለሰማዕት ወእጎቶሙ ለመላእክት
ቃልኪ አዳም ይጥዕመኒ እምአስካለ ወይን
ትርጉም፦ የሰማዕታት እናታቸው የመላእክትም እኅታቸው
ያማረ ቃልሽ ከወይን ፍሬ ይልቅ ይጣፍጠኛል

66. በጽሐ ሠናይ */ወ/ሮ ሰዳነች አስፋው/*

በጽሐ ሠናይ ወአልፀቀ ዘመን /፪/ ወበዓላ ለቅድስት ማርያም /፪/
እንተ በላዕሌሃ ተመርዓወ ቃል አንጺሖ ሥጋሃ ላዕለሃ ሀደረ
ትርጉም፡ – ቃል ሥጋዋን አንጽቶ ያደረባትና የተሞሸረባ የቅድስት ማርያም
የክብረ በዓሏ ዘመን ወቅት በሰላም ደረሰ ገባ::

67. ጽላት ዘሙሴ

ጽላት ዘሙሴ ዕፀ ጳጦስ ዘሲና /፪/
ጸናጽል ዘውስተ ልብሱ ለአሮን ካህን /፪/
ትርጉም፦ የሙሴ ጽላት ጳጦስ የተባለች የሲና ዕፅ
በካህን አሮን ልብስ የነበረች ጸናጽል እርሷ ነች

68. ዘየሀይድ ዓይነ

ዘየሀይድ ዓይነ /፪/ ልበሰ ክበር ለቢሶ ዳዊት /፪/
ቅድመ ታቦተ ሕግ ጎለየ ቅድመ ታቦተ ሕግ /፪/
ትርጉም፡ ዳዊት ዓይን የሚሰውር /የሚያብረቀርቅ/ ልብስ ለብሶ
በታቦተ ሕግ /ታቦተ ጽዮን/ ፊት ዘመረ

69. እመ ብርሃን

እመ ብርሃን ወእመ ሕይወት /፪/
ማርያም ዘበአማን /፬/ ኧኸ
ትርጉም፡ የብርሃን እናት የሕይወት በእውነት ድንግል ማርያም ናት

70. ለመኑ እነግር ኃዘነ ልብየ

ለመኑ እነግር ኀዘነ ልብየ እንበሌኪ ማርያም እግዝእትየ /፪/
ወፍጡነ /፪/ ስምዕኒ ጸሎትየ /፬/

ትርጉም፡ - እመቤቴ ማርያም ሆይ የልቤን ሀዘን ከአንቺ በቀር ለማን
እነግራለሁ ፈጥነሽ ጸሎቴን ስሚ::

71. ሙሴኒ ርእያ */ኦኮቴት ቁ.1/*

ሙሴኒ ርእያ /፪/ ሀገር ቅድስት /፪/
እዝራኒ ተናገራ /፪/ ዘመራ ዳዊት /፪/
ትርጉም፡ - ሙሴ ያያት ዕዝራ የተናገረላት ዳዊት የዘመረላት ቅድስት ሀገር::

72. ልዑል ሠምራ

ልዑል ሠምራ ዳዊት ዘመራ /፪/
በቤተ መቅደስ ተወክፍዋ /፬/
ልዑል ወደዳት ዳዊትም ዘመረላት /፪/
በቤተ መቅደስ ተቀበሏት /፬/

73. ኦ ማርያም */ብዙኅየሁ ቁ.1/*

ኦ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ ወነአብየኪ /፪/
እስመ ወለድኪ ለነ መብልዓ ጽድቅ ዘበአማን ወስቴ ሕይወት ዘበአማን /፪/
ትርጉም፡- ማርያም ሆይ ስለዚህ እንወድሻለን ከፍ ከፍም እናድርግሻለን
እውነተኛውን መብል እውነተኛውን የሕይወት መጠጥ ወልደሽልናልና

74. ኦ ድንግል

ኦ ድንግል አኮ በተላህዮ ዘልህቂ ከመ አዋልደ
ዕብራውያን እለ ያገዝፉ ክሳዶን /፪/
አላ በቅድስና ወበንጽሕ ውሰተ ቤተ መቅደስ ነበርኪ ውሰተ ቤተ መቅደስ /፪/
ትርጉም፡ ድንግል ሆይ አንገታቸውን እንደሚያገዝፉ የዕብራውያን ሴቶች
ልጆች በዋዛ በፈዛዛ ያደግሽ አይደለም በንጽሕና በቅድስና በቤተ መቅደስ ኖርሽ እንጂ::

75. እንዘ ዘልፈ */ሰ.ት/ቤ.ት.ማ.ቁ.3/*

እንዘ ዘልፈ ትነብር ውስተ ቤተ እግዚአብሔር /፪/
አስተርአያ መልአክ ዘኢኮነ /፪/ ከመቀዲሙ ኢኮነ /፪/
ትርጉም፡- በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ዘወትር ስትኖር
እንደፊተኛው ያልሆነ መልዓክ ተገለጠላት

76. በሰላም ንዒ */ፋንቱ ወልዴ እና ይልማ ይሱ/*

በሰላም ንዒ /፪/ ማርያም /፪/
ትናዝዘኒ /፪/ ኀዘነ ልበየ
አዝ----------
ምስለ ሚካኤል /፪/ ወገብርኤል
አዝ----------
ምስለ ሱራፌል /፪/ ወኪሩቤል
አዝ----------
ምስለ ዑራኤል /፪/ ወሩፋኤል
አዝ----------
ምስለ ኩሎሙ ፪/ ቅዱሳን
አዝ----------
ምስለ ወልድኪ /፪/ አማኑኤል
አዝ----------/፪/

77. አስተርእዮ በሰማይ ኮነ */ሰ.ት/ቤት.ማ.ቁ.3/*

ሐዋርያት ሁሉ አዘኑ ተከዙ
በስብሐት በማህሌት ሥጋዋን ገነዙ
አስተርእዮ በሰማይ ኮነ አስተርእዮ/፪/
በክብር በስብሐት መላእክት በራማ
እያመሰገኗት በጥዑም ዜማ
የማትፈቅጂ ድንግል የኃጥአንን ሞት
በአማላጅነትሽ አቆዩን ጥቂት
የምታምር ርግብ ሰሎሞን አለሽ
ሥጋሽን ለመልበስ ወልድ መረጠሽ
ሞትንስ መሞትን ለሁሉም ይገባል
የድንግል መሞት ግን በጣም ያስደንቃል
አዝ-------/፪/

78. ኪዳንኪ ኮነ

ኪዳንኪ ኮነ /፪/ ኪዳነ ምሕረት /፬/
ለኃጥአን ተስፋ ለኃጥአን ቤዛነ ኪዳንኪ ኮነ /፬/
ትርጉም፦ ቃል ኪዳንሽ የምሕረት ቃል ኪዳን ሆነ ለኃጥአን ተስፋቸው ሆነ

79. ፀቃውዕ

ፀቃውዕ /፬/
ይውጎዝ እምከናፍሪሃ /፬/
ትርጉም፦ የማር ወለላ /ጣፋጭ ነገር/ ከከናፍሮቿ ይፈስሳል /ከእመቤታችን

80. ዕፀ ጳጦስ ዘሲና */በመ/መ/ ቅ/ገብርኤል ገዳም ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት ቁ.2/*

ዕፀ ጳጦስ ዘሲና ማርያም
የኖኅ ድንቅ መርከብ ተስፋው የአዳም
አምላክ ያስቀረልን ንጽሕቷ የአዳም ዘር
እናወድስሻለን እንድናገኝ ባንቺ ክብር
ወርቅ ተጎናጽፈሽ በልዑል ቀኝ የምትቆሚ
ምሳሌ የሌለሽ አዛኝቱ እኛን ስሚ
የአቤል የዋህነት የሴት ቸርነት
የሴም ቡራኬው ነሽ የአብርሃም እንግድነት
የይስሐቅ መዓዛ የያዕቆብ መሰላል
የአሮን ካህን ልብስ የወርቅ ጸናጽል
የሳሙኤል ሙዳይ የጌዴዎን ፀምር
የኢያሱ ሐውልት የአሮን በትር
የሰሎሞን አክሊል የአሚናዳብ ሠረገላ
የኤልሳዕ ማሰሮ የኃጥአን ከለላ

81. ክብረ ቅዱሳን

ክብረ ቅዱሳን ይእቲ /፪/ ማርያም /፪/
ሙዳየ መና ግሩም ሙዳየ መና /፪/
ትርጉም፣ የቅዱሳን ክብር የመና ሙዳይ ማርያም አንቺ ነሽ

82. ዕፀ ጳጦስ ይእቲ

ዕፀ ጳጦስ ይእቲ እንተ በአማን ይብልዋ ቅድስተ ቅዱሳን /፪/
ሰአሊ ለነ ማርያም እም አምላክ አንቀጸ ብርሃን /፪/
ትርጉም፣ ቅድስተ ቅዱሳን የሚሉሽ ዕፀ ጳጦስ በእውነት አንቺ ነሽ ይሏታል።
ለምኝልን ማርያም የአምላክ እናት የብርሃን መውጫ

83. ንጽሕት ቅድስት */ዲ/ን ታደሰ ፊጣ ቁ.1/*

ንጽሕት ቅድስት የተመረጥሽ
የመንፈስ ኃይል የጸለለሽ
የእግዚአብሔር ቃል ያደረብሽ
ለእኛ ሕይወት መዲና ነሽ
ቅድስት ማርያም ክብርት ነሽ በጣም /፫/
ምልዕተ ፀጋ እናታችን
ልዕልት ነሽ እመቤታችን
የሕይወት አምባ መጠጊያችን
የዘለዓለም አለኝታችን
አዝ.....
ኖኅተ ምሥራቅ የአምላክ መንበር
የሕይወት ቤዛ ድንቅ ምስጢር
የኃጥአን ተስፋ የአምላክ ሀገር
ቅድስት ነሽ የእኛ ክብር
አዝ.....

84. ለሳውል ወኬፋ

ለሳውል ወኬፋ /፬/
አክሊሎሙ /፪/ ትኩነነ ተስፋ /፬/
ትርጉም፦ የጴጥሮስና የጳውሎስ አክሊላቸው ድንግል ማርያም ተስፋ ትሁነን።

85. ትርሲተ ወልድ

ትርሲተ ወልድ መለኮት ወፍቅር ኃደረ ላዕሌሃ ኃደረ /፪/
ይቤላ ርግብየ ወይቤላ ሠናይትየ ማርያም ድንግል /፪/
ትርጉም፦ ጠቢቡ ሰሎሞን ያማረች ርግቤ ያላት እመቤታችን ድንግል ማርያም መለኮታዊ የሆነውና ይህንን ዓለም በፍቅሩ የወደደው በእርሷ ላይም ያደረው የወልድ ሽልማት ናት።

* ነሐሴ 16 የሚዘመር

86. የዓለም ንግሥት የሆንሽው

የዓለም ንግሥት የሆንሽው
ድንግል ማርያም እናቴ
ታመስግንሽ አንቺን ሁል ጊዜ ሕይወቴ
ማርያም ባርኪኝ እመቤቴ እሰግድ ለኪ
እንዳልንገላ ጠብቂኝ በ ጢአት ዓለም ጎዳና
ደግሞም እንድመገብ ሰማያዊ መና

ማርያም የአዳም ጤና አሰግድ ለኪ
ተሸጩ ስኖር ልጅሽ በ ጢአት ዓለም ከተማ
የሚያወጣኝ ጠፍቶ የእናት ልጅ ወንድም
ወጣሁኝ በልጅሽ ደም እሰግድ ለኪ
የአንቺ መንገላታት ሁሉ ጊዜ ያሳዝናኛል ሲወራ
ማር ነፍሴን አደራ አሰግድ ለኪ

መዝሙር በእንተ ብሥራት

87. ማርያም ደስ ይበልሽ

ማርያም /፫/ ደስ ይበልሽ በገብርኤል ሰላምታ
በአንቺ ስላደረ የዓለም ሁሉ ጌታ /፪/
የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን
ጨለማው ተገፍፎ ሲመጣ ብርሃን
መድኃኒት ሲመጣ ሰይጣን እንዳፈረ
የዜናው አብሣሪ ገብርኤል ነበረ
አዝ----------
ድንግል ተቀምጣ በቤተ መቅደስ
ሐር ወርቅ አስማምታ ስትፈትል ንግሥት
ገብርኤል /፪/ ዜናዊ ሐዲስ
የአምላክን መወለድ ሥጋ በመልበስ
አዝ----------
ገብርኤል ሲያበሥራት ድንግል ስትሰማ
በእርሷ ላይ አረፈ የመለኮት ግርማ
እውነተኛ መልአክ መሆኑን ስላየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች
አዝ----------

88. አብሠራ ወይቤላ */ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ተ/ቢት ቁ.2/*

አብሠራ ወይቤላ ለማርያም ገብርኤል አብሠራ መልአክ /፪/
አልቦ ማኅለቅት ለሰላሙ ዲበ መንበረ ዳዊት መንግሥቱ ትፀንዕ /፪/
ትርጉም፡- መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን አበሠራት ካንቺ
የሚወለደው ለሰላሙ ፍፃሜ የለውም አላት መንግስቱ በዳዊት መንበር ላይ ትፀናለች

መዝሙር በእንተ ልደታ ለማርያም

89. አልብኪ ነውር

አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ በላዕሌኪ /፪
ፃኢ እምሊባኖስ እኅትየ መርዓት /፬
የለብሽም ነውር ምንም ነገር በላይሽ ላይ /፪
ውጪ ከሊባኖስ እህቴ ሙሽራ /፬

90. አዕይንታ ዘርግብ

አዕይንታ ዘርግብ /ፏ/ ኢያቄም ወለዳ /ፏ
ኢያቄም ወለዳ /ቿ/ ዘርግብ ኢያቄም ወለዳ ኧኸ /ቮ/
ትርጉም፦ አይኖቿ የርግብ የመሰሉ /የሆኑ/ ልጅን ኢያቄም ወለደ።

91. ተወለደችልን /ማኀ/ቅ/ቁ ፭/

ተወለደችልን ድንግል ማርያም
የነቢያት ትንቢት ሕይወተ አዳም
ሐናና ኢያቄም በጸሎት ሲተጉ
የአምላክን ስጦታ ፀንተው ሲፈልጉ
በሕግ በሥርዓት ሆነው ሲማልዱ
የጸሐይን እናት ሰማይን ወለዱ
አባቶች ነቢያት ያደረጓት ተስፋ
ምልክት የሆነች በሞት እንዳንጠፋ
የቀረችልን ዘር የአምላክ መገኛ
የሕይወት ውሃ ምንጭ ተወለደች ለእኛ
የጥል ምክንያት ብትሆን ሔዋን
በድንግል መወለድ እርቅ ሆነልን
ለአዳም ዘር ሁሉ መድኃኒት ናትና
እናቱን የሰጠን ይድረሰው ምስጋና

መዝሙር ዘዘመነ ጽጌ

92. አክሊለ ጽጌ

አክሊለ ጽጌ ማርያም ቀፀላ መንግሥቱ ለጊዮርጊስ
ክበበ ጌራ ወርቅ /፱/ አክሊለ ጽጌ
ትርጉም፦ በአበባ የተሸለመ አክሊልን የወርቅ ዘውድንም የምታቀዳጂ
ማርያም ሆይ የጊዮርጊስ የመንግሥቱ አክሊል /የነገሠብሽ አክሊል/ ነሽ

93. ረሀበ ወጽምዓ

ረሀበ ወጽምዓ አዘክሪ ድንግል ረሀበ ወጽምዓ /፱/
ምንዳቤ ውኀዘነ አዘክሪ ድንግል /፱/
ትርጉም፦ ድንግል ሆይ ረሀቡንና ጥሙን ችግሩንና ኃዘኑን አሳስቢ

94. ንግሥት እመቤቴ

ንግሥት እመቤቴ ድንግል ማርያም
ካንቺ ጋር ተራበ መድሃኔዓለም
ከገነት ተሰዶ እንዳይቀር አዳም
አንቺ ተንገላታሽ ከህፃንሽ ጋራ
ባልበደልሽው በደል አገኘሽ መከራ
አንቺ ንግሥት ስትሆኝ የሁሉ እመቤት
ሄሮድስ ዳረገሽ አንቺን ለስደት /፱/

እንዴት አደረገሽ ረሀብ እና ጥሙ
ዋዕዩና ብርዱ እንዲሁም ድካሙ
ልጅሽ መድሃኔዓለም ሁሉን ማድረግ ሲችል
ተሠደደ ለእኛ ካንቺ ጋራ ድንግል
ተሠደድሽ ድንግል በግብፅ በረሃ
ለሦስት ዓመት ከሳድስ አውራሃ
እንዴት አለቀልሽ የበረሃው ቦታ
የጨለማው ጥልቀት የአራዊት ሁካታ
እንግዲህ ጠብቂኝ ድንግል የእኔ እመቤት
ተሠድጄ እንዳልቀር ከዘለዓለም ሕይወት
ጨምሪልኝ እድሜ በጎ እንድሠራበት
ለንስሐ አብቂኝ በነፍሴ እንዳልሞት /፫/

95. አፈ ንህብ

አፈ ንህብ ማቱሳላ ወልደ ሔኖክ እምአፈ ልምላሜ ቡሩክ አፈ መልአክ /፪/
ቀሰመ ጽጌ /፪/ ጽጌኪ እመ እምላክ
ትርጉም፦ አፈንብ የተሰኘ የሄኖክ ልጅ ማቱሳላ
የአምላክ እናት ሆይ ከቡሩክ ልምላሜ አበባሽ ቀሰመ።።

96.ክበበ ጌራ ወርቅ

ክበበ ጌራ ወርቅ /፬/
አክሊለ ጽጌ ማርያም /፬/
ትርጉም፦ ድንግል አንቺ የአበባ አክሊልና የወርቅ ማርዳ ነሽ።።

97.መዓዛ አፈዋት */ሰ.ት/ቤት.ማ.ቁ.2/*

መዓዛ አፈዋት ማርያም /፪/ ጽጌ መንግሥት ቡርክት /፪/
ጽጌ /፪/ ዘሰሎሞን ወዳዊት አብርሃ ወአጽብሐ /፪/
ትርጉም፦ በጎ መዓዛ ያለሽ ሽቱ /ቅመም/ የተባረክሽ የመንግሥት
/የክብር/ አበባ ማርያም የሰሎሞን የዳዊት የአብርሃና የአጽብሃ ክብራቸው ነሽ::

98.ጎብረ ሐመልሚል

ጎብረ ሐመልሚል ቀይህ ወጸአድኢድ /፪
ተፈፀመ /፫/ ማኅሌተ ጽጌ /፪
ትርጉም፦ ቀይ ና ነጭ የሆነ የልምላሜ ምስጋናሽ ድንግል ሆይ ተፈጸመ።።

99.ሰላም ለኪ

ሰላም ለኪ /፫/ /፪
ክበበ ጌራ ወርቅ /፪/ አክሊለ ጽጌ
ትርጉም፦ የወርቅ ማርዳ ሆይ ሰላምታ ላንቺ ይገባሻል::
የአበባ አክሊል የቅዱሳን ክብር ነሽ::

100. ጽጌ አክሊለ ጽጌ

ጽጌ /፪/ አክሊለ ጽጌ /፪/ ማርያም /፪/ ኧኸ
ክበበ ጌራ ወርቅ /፪/ አክሊለ ጽጌ

ትርጉም፣ *ማርያም ሆይ የአበባ አክሊል የወርቅ ማርዳ ነሽ::*

101. ክበበ ጌራ ወርቅ ጽሩይ

ክበበ ጌራ ወርቅ ጽሩይ ክበበ ጌራ ወርቅ /፪/ ኧኸ
እም እንቄ ባሕርይ /፪/ ዘየሀቱ /፪/ ጽሩይ እም እንቄ ባሕርይ /፪/ ኧኸ
ትርጉም፦ በወርቀ ዘቦ ያጌጠ ከተመረጠ ከሚያበራ ዕንቁ ይልቅ የሚበራ
ንጽህናሽ ከባህርየ ዕነቁ ይልቅ የሚያበራ ነው::

102. እንዘ ተኃቅፊዮ

እንዘ ተኃቅፊዮ ለሕፃንኪ ንዒ ማርያም /፪/
ንዒ /፫/ ማርያም /፬/
ትርጉም፣ ህፃንሽን ታቅፈሽ ማርያም ነይ

መዝሙር በእንተ መስቀሉ ለእግዚእነ

103. መስቀሉሰ

መስቀሉሰ ለክርስቶሰ ብርሃን ለእለ ነአምን ትብል ቤተ ክርስቲያን /፪/
ዛህኑ ለባሕር ወመርሶ ለአሕማር ዝንቱ ውእቱ መስቀል /፪/
ትርጉም፦ የክርስቶስ መስቀል ለምናምን ሰዎች ብርሃን ነው
መስቀል የባሕር ፀጥታው የመርከቦች ወደብ ነው ትላለች ቤተ ክርስቲያን

104. ቤተ ክርስቲያን ርእየቶ

ቤተ ክርስቲያን ር የቶ ቅንወ ለዘበጎልጎታ ደሙ ተክዕወ /፪/
ከመ እግረ ፀሐይ ሥኑ ኀተወ በዓለ መስቀል ዘዮም ትገብር ህልወ /፪/
ትርጉም፦ በጎልጎታ ደሙ የፈሰሰውን አምላክ ቤተ ክርስቲያን አየችው
ደም ግባቱም እንደ ፀሐይ አውታር /ጮራ/ አበራ የዛሬው የመስቀል
በዓልም ለዘለዓለም ታበራለች

105. ዝንቱ መስቀል

ዝንቱ መስቀል ኀብስተ ሕይወት አፍረየ አውኀዘ ለነ ደመ ወማየ አውኀዘ ለነ /፪/
ከመ ጌራ ወርቅ ጽሩይ ሥርግው በባህርይ መስቀል ነቢሮ ያስተርኢ ላዕለ ርዕስየ /፪/
ትርጉም፦ ይህ መሰቀል የሕይወት ኅብስትን /አስገኝልን/ ደምና ውኃንም አመነጨልን
በዕንቁ እንደ ተሸለመ እንደ ንጹሕ የወርቅ አክሊል /ዘውድ/ መስቀል በራሴ ላይ
ሆኖ ያበራል:: /ሥጋውን ደሙን በመስቀል ተሰቅሎ እንደሰጠን ለመናገር ነው/

106. እንተ ተሐንፀት በስሙ

እንተ ተሐንፀት በስሙ ወተቀደሰት በደሙ ቤተክርስቲያን /፪/
ወተአትበት በዕፀ መስቀሉ እስመ ኃይለ እግዚአብሔር ላዕሌሃ /፪/
ትርጉም፦ በስሙ የታነፀች /ያመነች/ በደሙም የተቀደሰች /የከበረች/
በመስቀሉም የታተመች ቤተ ክርስቲያን /ምእመን/ የእግዚአብሔር
ኃይል በራሷ ላይ አለ::

107. ኧኸ በመስቀልከ

ኧኸ በመስቀልከ ኧኸ ጽልመተ አብራህክ
ኧኸ በመስቀልከ ኧኸ ሙታነ አንሣእከ /፪/
እኸ ወዘተ ጉለ ረዳእከ በመስቀልከ/፪/
ትርጉም፦ በመሰቀልህ ጨለማን አበራሀ ሙታንንም አነሣሀ
የጠፋውንም በመስቀልህ ረዳኸው/አዳንኸው/::

108. ዘዕጣን አንጸረ

ዘዕጣን አንጸረ /፬/
በጎልጎታ ተረክበ ዕፀ መስቀል /፬/
ትርጉም፦ ዕጣኑ አመለከተ መስቀሉ በጎልጎታ ተገኘ::

109. ይቤሎሙ ኢየሱስ

ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአይሁድ እመኑ ብየ /፪/
ወእመኑ በአቡየ <u>አበርህ</u> /፪/ በመስቀልየ /፪/
ትርጉም፦ ጌ ኢየሱስ አይሁድን በ ኔ ዕመኑ በአባቴ መኑ
ላመኑብኝ በመስቀሌ አበራለሁ አላቸው::

110. መስቀል ቤዛ ብዙኃን

መስቀል ቤዛ ብዙ ን ሕይወተ ኮነ ለኩሉ ዓለም /፪/
ፍስሐነ ወሰላምነ ለእለ አመነ መሠረተ ቤተክርስቲያን /፪/
ትርጉም፡ የብዙኃን ቤዛ መስቀል ለዓለም ሹሉ መድኃኒት ኾነ::
ለምናምን ደስታችን ሰላማችን የቤተ ክርስቲያን መሠረት ነው::

111. ዮም በዓለ መስቀሉ

ዮም በዓለ መስቀሉ በሰማያት በላዕሉ /፪/
<u>ወዘነግሠ በምድር</u> /፪/ ለአሕዛብ /፬/ ኧኸ
ትርጉም፡ ዛሬ በላይ በሰማያት የመሰቀል በዓል ነው፤
ለአሕዛብም በምድር ነገሠ::

መዝሙር በእንተ ቅዱሳን መላእክት

112. እግዚኡ ረሰዮ

እግዚኡ ረሰዮ ለውእቱ ሚካኤል /፪/
እምኩሉሙ <u>መላእክት</u> /፪/ ይትሌዐል መንበሩ
ትርጉም፦ ጌታው ሚካኤልን ከመላእክት ሁሉ መንበሩን ከፍ ከፍ አደረገው::

113. ሊቃነ መላእክት /በመ/መ/ ቅ/ገብርኤል ገዳም ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት ቁ.፬

ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል
ሰይጣንን ድል ያደረግህ በፈጣሪ ኃይል

የኃይላት አለቃ የትጎትና መልአክ
እናመስግን አንተን አፎምያን ያዳንክ

ኃያሉ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል
ልደትን ያበሠርክ ለማርያም ድንግል
መልአከ ብሥራት መልአከ ብሥራት
መልአከ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል

ፈታሔ ማኅፀን ቅዱስ ሩፋኤል
የሰዎችን ችግር ፈጥነህ የምታቀል
በአንተ አማላጅነት ፈጣሪን ስንለምን
ቶሎ ድረስና ረድኤትህን ስጠን

መጋቤ ብርሃናት ቅዱስ ራጉኤል
ለምስጋና ትጉህ ቀን ሌሊት ሳትል
ሥዕልህ ፊት ቆመን አንተን ስንማፀን
እዘንልንና ገጽህን አብራልን

ቅዱስ ዑራኤል ሊቀ መላእክት
ኢትዮጵያን የባረክህ በድንግል ስደት
መልአከ ሰላም ነህ መልአከ ሰላም
በመስቀልህ ባርካት ይህችን ዓለም

ቅዱስ ፋኑኤል ብርሃናዊ መልአክ
ሰማያዊ ጎብስት ለድንግል የመገብክ
በነፍስ በሥጋ ረ ብ ጠውልገን እንዳንደርቅ
ምልጃህ አይለየን በሲያል እንዳንወድቅ

ባሕርና ወንዝ በልክ እንዲሞሉ
ዝናብ የምታሰጥ ለዓለም በሙሉ
በኃጢአት እንዳንወድቅ ፍሬ ሳናፈራ
ቅዱስ ሳቁኤል ሆይ ጠብቀን አደራ

114. የራማው ልዑል /በመ/መ/ ቅ/ገብርኤል ገዳም ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት ቁ.1/

የራማው ልዑል ገብርኤል /፪/
ተመላለስ መሐላችን ስምህን ጠርተን ና ስንልህ /፪/
ብርሃን ልብሱ እሳታዊው መልአክ
አንተ አማልደን ከመሐሪው አምላክ /፪/
የምሥራች ነጋሪ ድንቅ ልደት አብሣሪ
የጽድቅ ፋና የድኅነት ጎዳና /፪/
ላመኑብህ ለተማፀኑብህ
ፈጥኖ ደራሽ አለኝታቸው ነህ /፪/
የአናንያ የአዛርያ የሚሳኤል ከለላቸው
ከእሳት ነበልባል ያዳንካቸው /፪/
ምሰሶ ዓምዳችን መጠጊያችን
ቅዱስ ገብርኤል ጠባቂያችን /፪/

115. ገብርዔል ግሩም

ገብርኤል ግሩም በመንፈስ ቅዱስ ጎቱም /፪/
ነዓ /፬/ ማዕከሌነ ቁም በበዓልከ ባርከነ ዮም
ትርጉም፦ በመንፈስ ቅዱስ የታተምህ ኃያል ገብርኤል ሆይ
በበዓልህ ቀን ትባርከን ዘንድ ና በመካከለችን ቁም

116. ገብርኤል መልአክ

ገብርኤል መልአክ ወረደ ኀበ ቂርቆስ ወእሙ <u>ኢየሉጣ</u> /፪/ ቅድስት
ዘአጥፍኦ ለነበልባለ እሳት ዘአድ ኖሙ ለሰማዕት /፪/
ትርጉም፦ ሰማዕታትን ያዳናቸውና የእሳቱን ነበልባል ያጠፋው
ገብርኤል ወደ ቂርቆስና እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ ወረደ።።

117. ፍቁራኒሁ

ፍቁራኒሁ ለአብ ሐራን መተንብላን /፪/
እለ ይስእሉ ምሕረተ ለውሉደ ሰብእ ሱራፌል ወኪሩቤል /፪/
ትርጉም፦ አማላጆች ወዳጆች ርኅሩኆች ለሆኑ ለሰው ልጆች ምሕረትን
የሚለምኑ የአብ ወዳጆች ሱራፌልና ኪሩቤል ናቸው።።

118. ሱራፌል በግርማሆሙ

ሱራፌል በግርማሆሙ ወኪሩቤል በውዳሴሆሙ /፪/
ኀበ አንጻረ ቀዳማዊ የሐውሩ በሠረገላ ይረውጹ /፪/
ትርጉም፡ - ሱራፌል በግርማቸው ኪሩቤል በምስጋናቸው
በቀዳማዊው ፊት አንፃር በሠረገላ ይሮጣሉ /ይመላለሳሉ/።። ** ቀዳማዊ የሚቀድመው የሌለ ማለት ነው።።*

<u>መዝሙር በእንተ ቅዱሳን</u>

119. የምእመናን አባት

የምእመናን አባት አገልጋይ የአምላክ ባለሟል መርቆሬዎስ /፪/
ተቀበለ ዛሬ /፬/ አክሊለ ሰማዕታት /፪/ ኧኸ

120. ጸለዩ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ */ሰ.ት/ቤት.ማ.ቁ.3/*

ጸለዩ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ ኀበ ሥዕሉ ለቅዱስ መርቆሬዎስ /፪/
ደነነ ሥዕል /፪/ ዘመርቆሬዎስ ከመ አሆ ዘይብል
ወተፈሥሑ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ /፪/
ጸለዩ ባስልዮስና ጎርጎርዮስ ወደ ሥዕሉ ለቅዱስ መርቆሬዎስ /፪/
ዝቅ አለ ሥዕል /፪/ የመርቆሬዎስ አቤት እንደሚል
ተደሰቱ ባስልዮስ ጎርጎርዮስም /፪/

121. ይቤሎ ጴጥሮስ

ይቤሎ ጴጥሮስ ለጳውሎስ ጥባዕኬ እጎየ ጳውሎስ /፪/
ወኢትናፍቅ ኢንመውት ዳግመ እምዝ ዳግመ /፪/
ትርጉም፦ጴጥሮስ ጳውሎስን ወንድሜ ጳውሎስ ሆይ ጨክን
አትጠራጠር ከእንግዲህ ዳግመኛ አንሞትምና አለው

122. ተክለ ሃይማኖት ተወለዱ

ተክለ ሃይማኖት ተወለዱ እሰይ እሰይ /፪/
የዓለም ብርሃን /፪/ <u>የጽድቅ ፀሐይ</u> /፪/ ባለሟሉ የአምላክ አገልጋይ /፪/

123. አረጋዊ ምሉዓ ፍቅር

አረጋዊ ምሉዓ ፍቅር ከመ ጽጌረዳ ዘይወፅእ እም አፉሁ ዕጣነ ቅድስና /፪/
ለገቢረ ሠናይ ዘይወጽዕ ከመ ማይ ምስለ ገብረ ክርስቶስ /፪/
ትርጉም፦ከአንደበቱ እንደ ጽጌሬዳ የቅድስና መልካም ሽታ
/ቃል/የሚወጣ ፍቅርን የተመላ አረጋዊ ከገብረክርስቶስ
ጋር ለበጎ ሥራ እንደ ውኃ ይወጣል::

124. ደምፀ ወተሰብከ

ደምፀ <u>ወተሰብከ</u> /፪/ ውስተ ዓለም /፪/
ዜና ምግባሩ ትሩፍ ለአረጋዊ /፬/
ትርጉም፦ ትሩፋትን የሚሠራ የአረጋዊ የምግባሩ
የገድሉ ዜና በዓለም ተሰማ ተሰበከ::

125. ሰላም ለክሙ

ሰላም ለክሙ ጻድቃን ወሰማዕታት እለ አእረፍክሙ በሃይማኖት /፪/
መዋዕያነ ዓለም አንትሙ እስመ በብዙኅ ትዕግስት
ሰአሉ ቅድመ ፈጣሪ በኩሉ ሰዓት /፪/

ትርጉም፦ በሃይማኖት ሆናችሁ ያረፋችሁ ጻድቃን ሰማዕታት ፍቅር
ሰላምታ ይገባችኋል ዓለምን በብዙ ትዕግስት ድል የነሣችሁ እናንተ
ኹል ጊዜ በፈጣሪ ፊት ለምኑልን::

126. እስጢፋኖስ ሰማዕት

እስጢፋኖስ ሰማዕት ሊቀ ዲያቆናት በምእመናን የተሾምክ /፪/
የአምላክህን ትዕዛዝ በሥራ የፈፀምክ /፬/

127. ሰአለ ሥርየተ ኃጢአት

ሰአለ ሥርየተ ኃጢአት ለእለ ወገርዎ /፪
ወይቤ ሥረይ ሎሙ ዘንተ ኃጢአቶሙ /፬/
ትርጉም፦ ለወገኖቹ የኃጢአት ስርየት ለመነ ኃጢአታቸውንም ይቅር በላቸው አለ
/ቅ.እስጢፋኖስ/

128. እንዘ ይነብር በየማኑ */ደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ሰ/ት/ቤት ቁ.1/*

እንዘ ይነብር ለአብ በየማኑ ወይረፍቅ ውስተ ህፅኑ የማኑ ለአብ /፪/
ርዕየ ወልደ ርዕየ በዓይኑ እስጢፋኖስ /፪/ ምሉዓ ጥበብ /፪/
ትርጉም፦ ጥበብን የተሞላ እስጢፋኖስ ወልድን በአብ ቀኝ
ተቀምጦ በአብ እቅፍ /ዕሪና/ ሲመሰገን በዓይኑ አየው

129. ግሩማን መላእክት */ሰ.ት/ቤት.ማ.ቁ.3/*

ሃሌ ሉያ ግሩማን መላእክት ሱራፌል ወኪሩቤል እለ አክናፊሆሙ ነበልባል /፪/
ወረዱ ዮም ይትቀበሉከ በብሂል አማን ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገባሬ ኃይል /፪/
ትርጉም፡- ክንፎቻቸው ነበልባል የሆኑ የሚያስፈሩ መላእክት ሱራፌልና ኪሩቤል ገብረ መንፈስ ቅዱስ በእውነት ተአምረኛ /ገባሬ ኃይል/ ነህ እያሉ ሊቀበሉህ ወረዱ::

130. ዘአጽናእኮሙ */ሰ.ት/ቤት.ማ.ቁ.2/*

ዘአጽናእኮሙ ለእሙንቱ አበዊነ ለሄኖክ ወኤልያስ /፪/
አንተ አጽንአነ በመንፈስ ቅዱስ /፪/
ያፀናህኮው ለእነርሱ አባቶቻችንን ለሄኖክና ኤልያስ /፪/
አንተ አጽናን በመንፈስ ቅዱስ /፪/

131. ጎዲጎ ብእሲቶ

ጎዲጎ ብእሲቶ መኒኖ መንግሥቶ /፪/
ዘፈለሰ/፫/ መኒኖ መንግሥቶ /፪/ኧኸ
ትርጉም፣ ሚስቱን ትቶ መንግሥቱን ትቶ መነነ /ገብረ ክርስቶስ/

132. ጥምቀተ አምጽአ */ሰ.ት/ቤት.ማ.ቁ.2/*

ጥምቀተ አምጽአ ሕፅወ ንግሥት ለእሊአሁ
እምነበ ፊሊጶስ ድኅረ ተጠምቀ ለሊሁ
ሰላማ አቡነ አምጽአ ለነ በዕድሜሁ ለመድኃኒነ
ምስጢረ ደሙ ወሥጋሁ
ትርጉም፡-የንግሥቲቱ ጃንደረባ በፊልጶስ ዘንድ ራሱ ከተጠመቀ በኋላ
ጥምቀትን አመጣልን፤ አባታችን አቡነ ሰላማም በዘመኑ
የመድኃኒታችንን የደሙንና የሥጋውን ምስጢር አመጣልን::

133. ለባርኮትነ ንኡ

ሰላም ለክሙ እንጦንስ ወመቃርስ አቢብ ሲኖዳ ገብረ መንፈስ ቅዱስ /2/
ለባርኮትነ ንኡ ውስተ ጽርሐ ዛቲ መቅደስ
ተክለ ሃይማኖት አኖሬዎስ ኤዎስጣቴዎስ } 2
ሳሙኤል ተክለ አልፋ በብኑዳ ኪሮስ
ትርጉም፡- እንጦንስ መቃርስ አቢብ ሲኖዳ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሰላም ይገባችኋል
ተክለ ሃይማኖት አኖሬዎስና ኤዎስጣቴዎስ ሳሙኤል ተክለ አልፋ በብኑዳ ኪሮስ
ትባርኩን ዘንድ በዚች መቅደስ ኑ፤፤

134. በመንፈስ የሐውር

በመንፈስ የሐውር እም ኃይል ውስተ ኃይል /፪/
<u>ካህን /፪/ ወነቢይ</u> /፪/ ዮሐንስ መጥምቅ /፪/
ትርጉም፡- ከኃይል ወደ ኃይል በመንፈስ ሄደ ካህንና ነቢይ ዮሐንስ መጥምቅ

135. ያሬድ ካህን /ዕዝል ዜማ/

ያሬድ ካህን አንደበተ ማር
እውነተኛ መምህር

በጣፊጠ ዜማ በጠለቀ ምሥጢር
ለአምላኩ ሲዘምር
መላእክት በሰማይ ላይ
ቅዱሳንም በምድር
ይታዩት ነበር ሲዘምሩ በክብር /፪

136. በጽድቅ የሚያምኑብህ /ዕዝል ዜማ/

በጽድቅ የሚያምኑብህ ቅዱሳን በሙሉ
ካንተ ባገኙት ኃይል ሁሉን ያደርጋሉ
እስራኤልን መርቶ ሙሴ ከግብፅ ሲያወጣ
ቢከታተላቸው ፈርዖንም በቁጣ
ባሕሩን ከፍሎ ሙሴ ሕዝቡን አሻገረ
ከሠራዊቱ ጋር ፈርዖን ሰጥሞ ቀረ
አዝ...
ጎልያድ ሲፎክር ተማምኖ በኃይሉ
የሚገጥመው ጠፍቶ ሁሉም ፈርተው ሳሉ
ብላቴናው ዳዊት ከእረኝነት መጥቶ
በአንድ ጠጠር ጣለው በአምላኩ ስም ወጥቶ
አዝ...
የእግዚአብሔርን መንፈስ ደፍረው ሊያታልሉ
ሐናንያና ሚስቱ በሐሰት ሲምሉ
ልባቸውን አውቆ ጴጥሮስ ገሠጻቸው
በሞት ተቀሰፉ አንድ ሆነ ቀብራቸው
አዝ...
ጳውሎስና ሲላስ በእስር ቤት ተጥለው
ሲዘምሩ ሳለ መከራውን ችለው
ተናወጠ ወሕኒው እስከ መሠረቱ
በጸሎታቸው ኃይል ከእስራት ተፈቱ
አዝ...

መዝሙር በእንተ ጾም

137. አምላካችን ጾመልን

አምላካችን ጾመልን አርባውን ቀን /፪/
ምሣሌውን ሊሠጠን ምሣሌውን /፬/

138. ዘጾመ ወጸለየ

ዘጾመ ወጸለየ ወሠዓለ /፪/
እሙነ ይነሥእ ዕሴቶ /፬/
የጾመ የጸለየ የለመነ /፪/
እውነት ነው ዋጋውን ይቀበላል /፬/

መዝሙር በእንተ ንስሐ

139. አምላክ ሆይ ጠብቀኝ */ማኅ.ቁ፪/*

አምላክ ሆይ ጠብቀኝ
ጌታ ሆይ ጠብቀኝ ከጥፋት አድነኝ
የተቀደሰውን ካለሥፍራው ጥዬ
ፈጽሜ ሳልጠፋ በምግባር ጎስቁዬ
በሥጋዬ ድካም ነፍሴ ሳትዝልብኝ
ወደ እኔ ተመልከት ክንድህን ዘርጋልኝ
አዝ----------
መንገዳገድ በዝቶ እንዳልቀር ወድቄ
ከሕያው ማዕድህ እንዳልሄድ ርቄ
አምላኬ እረኛዬ ድምጽህን አሰማኝ
ቦታዬን ሳላውቀው ተኩላ እንዳይበላኝ
አዝ----------
በንስሐ ውሃ ሕይወቴን አንጽቼ
ሰላሜ እንዲመለስ ቃልህን ሰምቼ
አንድ አድርጌ ይዤ ምግባር ከሃይማኖት
አልጫው ሕይወቴ ይሁን ጣፋጭ ሕይወት
አዝ----------

140. ልመናዬን ስማኝ */ዲ/ን መገርሳ በቀለ/*

ልመናዬን ስማኝ ቃሌንም አድምጥ
እውነተኛው አምላክ ሰላምህን ስጥ
ክርስቲያኖች ሁሉ ትእዛዙን አክብሩ
ምስጋናን አቅርቡ ስገዱ ዘምሩ
የጌታን አመጣጥ ለዓለም ንገሩ
ደቀ መዛሙርቱ ወንጌል አስተምሩ
በመልካም የሚሄድ ጽድቅን የሚሠራ
የፈጣሪውን ስም በከንቱ የማይጠራ
ይጎበኛል በምድር በሰማዩም ሥፍራ
በቀኝ ይቀመጣል ከቅዱሳን ጋር
ስለ ጠላቶቼ በጽድቅህ ምራኝ
በጥል ቃል ከበቡኝ ተሰለፉብኝ
መሐሪ ይቅር ባይ መጠጊያ ሁነኝ
አንተ በቸርነት ይቅርታን ስጠኝ

141. ተነሡ እንዘምር */ተምሮ ማሰተማር ቁ.1/*

ተነሡ እንዘምር /፫/ ለአምላክ ባንድ ቃል
ሁላችንም እንጂ ወንድ ሴት አንበል
ተነሡ እንዘምር ለአምላክ ባንድ ቃል
የአምላክ ምስጋና ምን ያሳፍረናል
እንኳንስ እርሱና ሰው ይመሰገናል
ለሚያወርድልን ዝናመ ምሕረትን
ደግሞም ለሚሰጠን እክለ በረከትን

ሁሉንም በጊዜው ለሚሠጠን ጌታ
መዘመር አለብን ሁላችን በእልልታ

142. ስምዓኒ እግዚኦ ጸሎትየ */ሰ.ት/ቤት.ማ.ቁ.2/*

ስምዓኒ እግዚኦ ጸሎትየ
ወይብጻሕ ቅድሜከ ገዓርየ } /፪/
ወኢትሚጥ ገጸከ እምኔየ

በዕለተ ምንዳቤየ አጽምዕ እዝነከ ኃቤየ
አመ ዕለተ እጼውዓከ ፍጡነ ስምዓኒ } /፪/

አቤቱ ስማኝ ጸሎቴን
ጩኸቴም ይድረስ ከፊትህ ዘንድ } /፪/
አትመልስ ፊትህን ከእኔ ዘንድ

በመከራዬ ቀን አድምጥ ጆሮህን ወደ እኔ
በጠራሁህ ዕለትም በፍጥነት ስማኝ } /፪/

143. እንሂድ እንገስግስ / በመ/መ/ ቅ/ገብርኤል ገዳም ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት ቁ.2/

እንሂድ እንገስግስ ወደ አባታችን
ጠርቶናልና ርስቱን ሊያወርሰን
የዘለዓለም ሕይወት እንዳይቀርብን
ሀብታችን ቤታችን ይህ አይደለምና
እንጓዝ ወደ እርሱ በቀናው ጎዳና
ዓለምን ድል ነሥተን ወደ እሱ እንድንሄድ
ፈጥነን እንለፈው ጠባቡን መንገድ
አዝ----------
በመንገድ ላይ ሳለን በመገስገስ ላይ
ከጠላት ሥር ወድቀን ከአንተ እንዳንለይ
አቤቱ ጌታ ሆይ ኃይልህን ስጠን
ድል ነስቶ እንዳይገዛን ፀራችን ሰይጣን
አዝ----------
በወጥመድ ተይዘን መዛጃው ጠፍቶብን
ወድቀን እንዳንቀር እርዳን አምላካችን
ቤታችን ተዘግቶ መግቢያ አጥተን እንዳንቀር
እንለምንሃለን እንድትለን ይቅር

144. አማን በአማን */ደልማ ኃይሉ ቁ.3/*

አማን በአማን /፬/
አማኑኤል ተመስገን
ለዚህ ፍቅርህ ምን ልክፈልህ
ድብቁን ኃጢአት አንተ ብትገልጠው
ይቅር ብለኸኝ ባትሸፋፍነው
እንደ ሰው በቀል ቢኖርህ ጌታ
ለእኔ ኃጢአትስ የለውም ቦታ
በየደቂቃው ኃጢአት ስሠራ
ስሰርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ
አንተ ግን ፊትህ ምንም ቢቀየም
በቁጣ በትር አልገረፍከኝም

ምሕረትህን ልከህ አድነኝ ዛሬ
ታክቶኛልና በኃጢአት መኖሬ
ዓለም በኃጢአት እየሳበችኝ
በጽድቅህ ደስታ መኖር አቃተኝ
የኃጢአት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም
ውጤቱ መርሮ ፍዑም አይጥምም
እንደ በደሌ ስላልከፈልከኝ
ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ

145. ታዛዥህ ልሁን /ዕዝል - ማኅ/ቅ/ቁ 6/

ለቃልህ የምገዛ ትሁት ሠው እንድሆን
ለቀሪው ሕይወቴ ምራኝ መንገድህን
ዓለምና ውበቷ ማርከው እንዳይገዙኝ
ጉልበቴም እንዳይደክም ኃይልህን አጎናፅፈኝ
ሳትጎሰቁል ነፍሴ ሳትዝልብኝ
ሥጋዬን ጎስመህ መንፈሴን አቅናልኝ
ይዓይኔ ብርሃን ፈዞ ማየት ተሰኖኛል
የዓለም ጨለማ ፊቴን ከልሎኛል
በመስቀልህ ብርሃን ከጨለማ አውጣኝ
ገጸ ምሕረትህን ፈጥነህ ግለጥልኝ
ፍቅርህን አውቄ ለእኔ ያለህን
ፈቃድህን ልፈፅም ታዛዥህ ልሁን
ሁሉ ባይሠምርልኝ እንደ እኔ ምኞት
ለበጎ ነው ልበል ለእኔ ደኅንነት
ጥፋቴን የማትወድ ይቅር ትልኛለህ
ወደ አንተ እስክመለስ ትታገሰኛለህ
መሐሪ ነህና አዶናይ አባቴ
ከበደሌ አንጻኝ ደግሞም ከኃጢአቴ
አዝ----------

146. አትራቀን /አሪራይ/ /ማኅ/ቅ/ቁ፮/

አትራቀን እንዳንቀር ወድቀን
አባታችን ሆይ መሐሪ ይቅር ባይ
አውጣን ከሥቃይ
ደካሞች ነን እና
የጽድቁም ጎዳና ጠፍቶብናልና አትራቀን ------
ኃጢአታችን በዝቶ
በደላችንም በርክቶ
ቢያስከፋህም ከቶ
ስራችንን አይተህ
በደላችንን አስበህ
በእኛ ተቆጥተህ አትራቀን-------
ይቅር ባይ ነህና
የሀጥዑን ሞቱን አትፈልግምና
አትተወን እኛን
በሲያልም ጥልቅ ውስጥ አትበቀለን አትራቀን------

የአብርሃም የይስሐቅ
ጽድቃቸውን አስበህ
ማረን እባክህ
መንጋዎችህ እኛን
እንዳንቀር ጠፍተን
በጸድቅህ ጎብኘን አትራቀን----

147. ደካማ ነኝ እኔ */አራራይ/ ማኅ/ቅ/ቁ፮/*

አቤቱ ፈጣሪ የኃጥአን ተስፋ
እንዳልወድቅ ደግፈኝ በዓለም እንዳልጠፋ
የሠራዊት ጌታ ሰማኝ ጩኸቴን
በምሕረትህ ብዛት ደምስስ በደሌን

ደካማ ነኝ እኔ መጓዝ የተሳነኝ
ጠላት በዙሪያዬ ከቦ የሚያስጨንቀኝ
በሕግህ ለመኖር እኔ አልቻልኩምና
ፈታኜን ጣልልኝ ኃይል የአንተ ነውና

አንተን ማሳዘኔ በደሌም ቢበዛ
ባታገኝም ከእኔ የጽድቅ መዓዛ
በምሕረትህ ብዛት አንተ ይቅር በለኝ
ሥራዬን አትየው እኔ ደካማ ነኝ

ዘወትር አለቅሳለሁ ድካሜን አውቄ
መኖሬ ሲሰማኝ ከቃልህ እርቄ
በመንገድህ ምራኝ ፊትህን እንዳይ
ስለ እናትህ ብልህ ከእኔ አትለይ

148. በሰማይ የምትኖር አባታችን */ሲ.መ. ኪነ ጥበብ/*

በሰማይ የምትኖር አባታችን ስምህ ይቀደስ ይመስገን
መንግሥትህም ትምጣልን ፈቃድህም ይሁን
በሰማይ እንደሆነ እንዲሁም በምድር
የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን
የበደሉንን ይቅር እንድንል በደላችንን ይቅር በለን
ይቅር በሉ ይቅር እንድትባሉ
የሚለውን ቃል ኪዳንህን አስታውሰህ ወደ ፈተና አታግባን
ከክፉ ነገር አድነን ከክፉ ሰህተት
ያንተ ናትና መንግሥትም ኃይልም ክብርም ለዘለዓለም አሜን

149. ሃሌ ሉያ ሕያው ሆነህ የምትኖር

ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ሕያው ሆነህ የምትኖር
ሞትን ያሸነፍክ በሥልጣንህ
ክርስቶስ የእኛ ጌታ ለዳዊት በእውነት የማልህ
አቤቱ ወዴት ነው ምሕረትህ
የተራበች ነፍስ ትጠባበቃለችና ከተስፋህ
ለስምህ ምስጋናን በማቅረብ
እውነትህንም በማሠብ

የሰውን ፊት አይተህ የማታዳላ
መማለጃ የማትበላ
እውነተኛ ንጉሥ አንተ ነህና ክርስቶስ

150. እስመ ለዓለም ምሕረቱ

እስመ ለዓለም ምሕረቱ ምን ያደርግልኛል ብከብር
መልካም ካልሠራሁ ለእግዚአብሔር
መልካም ሥራ ነበር የሚያገናኘኝ ከፈጣሪዬ ጋር
እንቢ አለ ልቦናዬ እያደላ ለሥጋዬ እንዳልገናኝ ከጌታዬ
እባክህ አርመው ልቦናዬን ክፉ መሥራቱን እንዲመንን
ምን ያደርግለታል ቢከብር ነፍሱንስ ቢያከስር
እስከዚህ ነው ወይ ልፋቱ
የዚህ ዓለም ሰው በከንቱ

መዝሙር በእንተ ቤተ ክርስቲያን

151. የድሆች መጠጊያ */መ/ር ሰዳነች አስፋው ቁ.1/*

የድሆች መጠጊያ ቤተክርስቲያን /፪/
እነሆ ተደሰች ልጆችሽ መጣን /፪/
ሰላም ሰላም <u>የዘለዓለም ቤቴ</u> /፪/ } /፪/
ከአንቺ አልለይም እስከ ዕለተ ሞቴ }
ሰላም ላንቺ ይሁን ቤተ ክርስቲያን /፪/
በደሙ ያፀናሽ ኢየሱስ መድኅን /፪/
ቤተ ክርስቲያን ሆይ የአማንያን እናት /፪/
ወደ አንቺ ቀርበናል እንድናገኝ ሕይወት /፪/
ቅረቡ ምእመናን በአንድነት ሆናችሁ /፪.
እጆቿን ዘርግታ ልተቀበላቸሁ
ተነሥታለችና ቅድስት እናታችሁ
አዝ.....

152. እንኳን ደኅና መጣችሁ

እንኳን ደህና መጣችሁ /፪/
ወደ እኔ ወደ እናታችሁ
እጇን ዘርግቼ ስጠብቃችሁ
ወላጆቻችሁን እንድታከብሩ
አምላካችን <u>መናገሩ</u> /፪/
እንድትፈፅሙ ትዕዛዙን
እምቢተኞች <u>ባለመሆን</u> /፪/
የዕውቀት ገበያተኞች እንደመሆናችሁ
ምንም ጊዜ <u>ባይኖራችሁ</u> /፪/
ከሰኞ እስከ ዐርብ እየሠራን
እንጠያየቅ <u>በሰንበት ቀን</u> /፪/
እንደዚህ እኮ የምላችሁ

ቤተክርስቲያን ነኝ እናታችሁ /፪/
ስለመጣችሁ እናንት ልጆቼ
ታዩኛላችሁ ተደስቼ /፪/

153. ወደ ቤተ እግዚአብሔር

ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንሂድ ሲሉኝ /2
እንደ ዳዊት እንደ ንጉሡ ተደሰትኩኝ /2
መላእክት በሰማይ የሚያመሰግኑህ /2
አምላካችን ፈቃድህ ይሁን እንዘምርልህ /2
ሞትን አሸንፎ ለተነሳው ጌታ /2
ዘምሩለት ተቀኙለት በጧት በማታ /2
በመስቀል ላይ ሳለ ሲወጋ ጎኑን /2
ውሃና ደም አንድ ላይ ሆኖ ፈሰሰልን /2
በውሃው ተጠምቀን ደሙን ጠጥተን
መንግሥቱን እንድንወርስ ስላደረገን
ስሙ ይክበር ከፍ ከፍ ይበል የጌታችን
ስሙ ይክበር ከፍ ከፍ ይበል የአምላካችን

154. ሃሌ ሉያ አንጥላት

ሃሌ ሉያ አንጥላት አንራቃት
ቤተ ክርስቲያንን አንራቃት
በደለኛ አናድርጋት
በወልድ ውሉድ በክርስቶስ ክርስቲያን
ተብለን የአምላክን ልጅነት
እርሷ ናትና ያገኘንባት
ዛሬም በህይወት ሳለን እርሷው ናት መጠጊያችን
ኋላም በሞት ጊዜ ከዚህ ዓለም ስንለይ
እርሷው ናት የሁላችን ተቀባይ

መዝሙር በእንተ ክረምት (በክረምት የሚዘመር)

155. ሰማያት ዘመሩ */ማርታ ቁ.፫/*

ዝናማትም ዘነሙ ወንዞችም ሳረፉ /፪/
የአምላክን ጸጋ እያትረፈረፉ /፪/
ሰማያትም ዘመሩ በልዑል ቃሉ /፪/
የፍጥረታት ሁሉ መጋቢ አንተ ነህ እያሉ /፪/
ገበሬውም አረሰ ፈጣሪውን አምኖ /፪/
ዘርንም በተነ በምድር ላይ ከጎተራው ዘግኖ /፪/
ደመናትም ዓለምን ይዞራሉ /፪/
በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ዝናምን ሊያድሉ /፪/
በልምልሚ ተዋቡ ዕፅዋት አትክልቱ /፪/
ፍሬን ይሰጡ ዘንድ አብዝተው በጊዜው በወቅቱ /፪/

መሬትም ከእርሻ አድርጋ ውለታ /፪/
የላቡን የወዙን ከፈለች እንዳዘዘ ጌታ /፪/
ድካሙን ጥረቱን አምላክ ተመልክቶ /፪/
እንኳን ፍሬ ሰጠው አብዝቶ አድርጎ መቶ /፪/
ዝናምን ለዘር ለልምላሜ ፍሬ /፪/
የሰጠን አምላክ ይመስገን ይክበር በዝማሬ /፪/